# መጽሔት ተልእኮ

## ዘማኅበረ ቅዱሳን

ግንቦት ፳፻፲፮ ዓ.ም
፩ኛ ዕትም





ማኅበረ ቅዱሳን በማእከላት
(የመቱ ማእከል)



መልአከ ሰላም መምህር ታዬ አብርሃም
(ጋሽ ታዬ)

አዘጋጅ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን የሕዝብ ግንኙነትና ትብብር አገልግሎት ማስተባበሪያ

# ማውጫ


01 መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን

02 ትምህርተ ወንጌል

03 ግብረ ማኅበረ ቅዱሳን

04 የአኀት አበያተ ክርስቲያናት ተሞክሮ ዳሰሳ

05 ማኅበረ ቅዱሳን በማእከላት።

06 ቤተ አናግድ

07 ይናገራል ፎቶው

# 1. መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን

**"እንዲህ ዓይነቱ (ሰይጣን) ከጾምና ከጸሎት በቀር አይወጣም፡፡" (ማቴ 17፡21)**

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ መንግሥቱን፣ ግርማ መለኮቱን ገልጦ ከታቦር ተራራ በወረደ ጊዜ ጋኔን አድሮበት ክፉኛ ያሠቃየው የነበረውን ብላቴና ከፈወሰው በኋላ ቅዱሳን ደቀ መዛሙርቱ "እኛ ይህን ሰይጣን ማውጣት ያልቻልነው ለምንድን ነው?" ባሉት ጊዜ የተናገረው ኃይለ ቃል ነው፡፡ ይህን ብላቴና ጋኔን እንዴት ያሠቃየው እንደነበር አባቱ ሲናገር "በጨረቃ እየተነሣበት ክፉኛ ይሠቃያል፤ ብዙ ጊዜ በእሳት ብዙ ጊዜም በውኃ ይወድቃል።" ብሎ ነበር (ማቴ. ፲፯፥፲፭) ይህ ጋኔን ይህን ብላቴና ከሕፃንነቱ ጀምሮ ተቆራኝቶ ያሠቃየው ስለነበር በወንጌል ትርጓሜያችን አብሮ አደግ ጋኔን ተብሏል። "ዝንቱ ዘመድ ኢይወፅእ ዘእንበለ በጾም ወበጸሎት - ይህ አብሮ አደግ ጋኔን ካልጾሙ ካልጸለዩ አይወጣም።" (ትርጓሜ ወንጌል ገጽ 144)

ሰው ክቡር የሆነ የእግዚአብሔር ብቻ ማደርያ ነው። (2ቆሮ 6፡16፣ 1ቆሮ 3፡16) በመሆኑም ቅዱሳን መላእክት እንኳን ሰውን ይጠብቁታል እንጂ አያድሩበትም። ቅዱሳን መላእክት ከመጠበቅ አልፈው በማያድሩበት በሰው ልጅ ጋኔን ለምን ያድርበታል? ተብሎ ቢጠየቅ አያሌ ምክንያቶችን መስጠት ይቻላል። የመጀመሪያውና ዋናው ምክንያት ሰው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ወጥቶ ለሰይጣንና ለፈቃዱ በመገዛቱ ነው። መጽሐፍ "እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው።" ብሎ እንደተናገረ ሰው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ወጥቶ ለማይገባ ነገር ሲገዛ ለተገዛለት ነገር ተላልፎ ይሰጣል። (ሮሜ 1፡28) ለሰይጣንና ለአሠራሩ ለጥንቆላ፣ ለመተት፣ ለድግምት፣ ለግብረ ሰዶሙ፣ ለተንኮሉ፣ ለዘረኝነቱ ስንገዛ ከእግዚአብሔር ማደርያነት ይልቅ ለሰይጣን ማደርያነት ምቹ እንሆናለን።

የተወደዳችሁ የቤተ ክርስቲያን ልጆች! ጸያፍ ወደ ሆኑ ተግባራት የሚገፉን ሐሳቦች፣ ሰውና እግዚአብሔርን የሚያሳዝኑ፣ የሚያስደነግጡና ተስፋ የሚያስቆርጡ ንግግሮችን እንድንናገር የሚገፉን ነገሮች፣ በሥነ ልቡና ባለሙያዎች ምክር አልሽነፍ ያለ ውስጣዊ መታወኮች በማያቋርጥ ጾምና ጸሎት መፍትሔ እንደሚያገኙ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት እንደ አስተማረን ልብ በሉ።

ዛሬ ሀገራችንን አንዴ በጦርነት አዙሪት ሌላ ጊዜ በዘረኝነት ጦስ፣ እንዲሁም ጠርዝ በረገጡ አስተሳሰቦች እየወጠረ በአራቱም አቅጣጫዎች ደም እያፋሰሰ የሚያፍገመግማትና የሚያንደፋድፋት ጋኔን የሚለቃት ለእግዚአብሔር ያደርን እውነተኛ ክርስቲያኖች ሆነን በፍጹም ልባችን ስንጾም፣ ስንጸልይ ስለሆነ አምላካችን እንዲህ ዓይነቱን መንፈስ እንዲአርቅልን ወደ እርሱ ተመልሰን በተቀደሰና በተወደደ ጾም ሆነን እንለምነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ተምዝግቦ እንደምናገኘው በነነዌ ሰዎች ላይ የመጣው ጥፋት በጾም በጸሎትና በንስሓ ተወግዷል፡፡(ትንቢተ ዮናስ) በንጉሡ በአርጤክስስ ዘመን የነበሩ አይሁድም በንግሥቲቱ አስቴር አሳሳቢነት ባወጇት ጾምና ጸሎት ሞታቸው በሕይወት ኀዘናቸው በደስታ ስጋታቸው በደኅንነት ተለውጧል፡፡ (መጽሐፈ አስቴር) አምላካችንችም በነቢዩ ኢዩኤል ላይ አድሮ "አሁንስ ይላል እግዚአብሔር በፍጹም ልባችሁ በጾምም በልቅሶና በዋይታም ወደ እኔ ተመለሱ፡፡" ብሎ እንድተናገረ። (ኢዩ 2፡12)

ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች መተቻቸቱን፣ መዘላለፉን፣ በገባንም ባልገባንም ነገር ዝም ብሎ ከማውራቱ ተቆጥበን በዚህ የጾም ወቅት ሀገራችን ከገባችበት ቅርቃር ትወጣ ዘንድ ወደ አምላካችን ወደ ልዑል እግዚአብሔር በጾም በልቅሶ በዋይታም እንጩኽ፡፡ ብዙ ብዙ ተባለ፤ ችግር እንጂ የተረፈ አንዳች መልካም ነገር የለም፡፡ ዛሬ እንደሚስተዋለው በሀገራችን ላለው ላፈጠጠ ችግር ከእምነታችንም አልፎ የእምነታችን መሠረት የሆነው ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "በየቀኑ ስሙ እየተጠራ ለኢትዮጵያ ምን አመጣላት?" እያሉ በልዩ ልዩ የማኅበራዊ ሚድያ ሥርዓት (Platform) የሚተቹ ሰዎችን እየተመለከትን ነው፡፡

ነገር ግን ጾምና ጸሎት እንዲሁም ወደ እግዚአብሔር በንስሓ መመለስ መፍትሔ ባያመጣ ኖሮ እግዚአብሔር "አሁንስ ይላል እግዚአብሔር በፍጹም ልባችሁ በጾምም በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ፡፡" ብሎ አያስተምረንም ነበር፡፡ የነነዌ ሰዎችም ታሪክ ሐሰት፣ በአስቴር ዘመን የተደረገውም ነገር የይስሙላ በተባለ ነበር፡፡ ስለሆነም ነቢዩ "መንገዳችንን እንመርምርና እንፈትን ወደ እግዚአብሔርም እንመለስ፡፡ ልባችንን ከእጃችን ጋር በሰማይ ወዳለው ወደ እግዚአብሔር እናንሣ፡፡" በማለት እንደመከረን ወደ እርሱ እንመለስ፡፡ (ሰቆ. ኤር. 3፥41)

የተወደዳችሁ የቤተ ክርስቲያን ልጆች! አምላካችን በመካከላችን ያለውን የመለያየትን፣ የጥፋትን፣ የዘርኝነትን፣ የአድመንኝነትን፣ የትዕቢትን፣ የድፍረትን፣ የሐሰትን፣ የምቀኝነትን፣ የዘማዊነትን መንፈስ (አብሮ አደግ ሰይጣን) ያርቅልን ዘንድ ለሀገራችን ሰላምና ፍቅርን ለቤተ ክርስቲያናችን ኀይለ መዊዕን እንዲሰጥልን ከምንጊዜውም በላይ ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት ሰዓት ስለሆነ በንስሓ ራሳችንን ዝቅ በማድረግ እንለምናው ዘንድ መልእክታችን ነው።

**የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን አማላጅነት የቅዱሳን በረከት አይለየን!**

# 2. ትምህርተ ወንጌል

## ርእስ፡ የትንሣኤ በረከቶች

**"እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ፤ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም።" ቆላ. ፫ ÷ ፩-፫**

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን። ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን አሰሮ ለሰይጣን አግዓዞ ለአዳም ሰላም እምይእዜሰ ኮነ ፍስሐ ወሰላም።

የልዑል እግዚአብሔር ቤተሰቦች እነሆ በብዙ መሻትና እና ጉጉት ስንጠብቀው የነበረ ከመርገመ አዳም ለመዳናችን ማረጋገጫ ወደሆነው የትንሣኤ ዘመን ያደረሰን ሁሉን የሚቻለው አምላካችን ስሙ የተመሰገነ ይሁን።

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን ያለው ቦታ እጅግ ታላቅ ነው። ምክንያቱም በኃጢአትና በሞት ላይ የተገኘ ታላቅ የድል የምሥራች በመሆኑ ነው።

ይህን የትንሣኤ ዘመን ያሳየን ዘንድ እግዚአብሔር አምላካችንን በታላቁ ጾም (በዐቢይ ጾም) ከጥሉላት ምግብ ከወትሮው ረዘም ላለ ጊዜ ተከልክለን፣ አገልግሎታችን ከከበሮና ከጸናጽል ተለይቶ ለጾም በተሠራ ማኅሌት፣ በምሕላ እና በስግደት እንዲሁም በጸሎት ስንማጸን ቆይተናል። ይህ ብቻ ሳይሆን የጌታችንን መውረድ እና መወለድ ከምናስብበት ዘወረደ ብለን ከምንጠራው ከመጀመሪያው ሳምንት ጀምሮ እስከ መጨረሻው የሕማማት ሳምንት ድረስ በቤተክርስቲያናችን አሳሳቢነት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በአንቃዕድዎ ልቡና ተጉዘናል። በፍጻሜውም በአምላካችን ቸርነት የትንሣኤውን ብርሃን ለማየት ችለናል።

ይህ የትንሣኤ ዘመን ለኛ ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኝ ክርስትያኖች ያለው ትርጉም ከፍተኛ ነው። ይኸውም ቀጥሎ ስለተጠቀሱት ምክንያቶች ነው።

### 1. በትንሣኤው መሠረተ ሃይማኖትን አገኘን።

የጌታችን ትንሣኤ ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ከምታስተምራቸው የዶግማ ትምህርቶች ውስጥ አንዱ ነው። ይኸውም የክርስቲያኖች ክርስቲያን መሆን ዋጋ የሚኖረው ከሞት ባለፈ ትንሣኤ ከትንሣኤያችው በኩር ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ መሆን ሲችሉ በመሆኑ ነው። ይህ ደግሞ የተረጋገጠው በመድኅን ክርስቶስ ትንሣኤ ነው። የእርሱ መነሣት የእኛን መነሣት እሙን እና እርግጥ(ላላ ብሎ ይነበብ) አድርጎታል። ያለ ጌታችን ትንሣኤ የምንመካበት እምነትም ሆነ ስብከት እንደሌለን ንዋይ ኅሩይ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ነግሮናል፡፡ "ክርስቶስ ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው። እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት።"(፩ኛ ቆሮ ፲፭ ÷ ፲፬) ስለዚህ እናት ቤተክርስቲያን ዓምድ ብላ ከምታስተምራቸው ትምህርቶች እንዱ የሆነው ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን በጌታ ትንሣኤ የተገኘ በረከት መሆኑን ልብ ይሏል።

## 2. በትንሣኤው የጌታችንን አምላክነት ፍጹም ተረዳን።

በቃል መነገሩ በልብ መዘከሩ ከፍ ከፍ ይበልና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን ዘወትር ቤተ ክርስቲያናችን ትመሰክራለች። የጌታችን አምላክነት በቅዱስ መጽሐፋችን በሰፊው የተገለጠ ቢሆንም ቅሉ በእርሱ ትንሣኤ ደግሞ ፍጹም ተሰብኳል(ተረጋግጧል)። ከጌታችን መነሣት አስቀድሞ ሌሎች አስቅድመው የተነሱ ነበሩ። ለምሳሌ፡- ጌታችን ይወደው የነበረው አልአዛር እና ጌታችን ተሰቅሎ በነበረበት ሰዓት መቃብር ተከፍቶ የተነሡ ሰዎችን መጥቀስ ይቻላል። ነገር ግን የጌታችን ትንሣኤ ከነዚህ መነሣቶች በሁለት ዐበይት ምክንያቶች ያለያል።

- የጌታ ትንሣኤ በታላቅ ኃይል እና በራሱ ሥልጣን የተደረገ፤ አስነሺ ያላስፈለገው በመሆኑ
- የጌታ ትንሣኤ ዳግም ሞት(የሥጋ እና የነፍስ መለያየት) የሌለበት ፍጹም መነሣት በመሆኑ

“ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደፊት እንዳይሞት ሞትም ወደፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና” (ሮሜ ፮ ÷ ፱)
ጌታችን አስቀድሞ ያደረጋቸው አምላክነቱን ያሳዩ ቢሆኑም ትንሣኤው ግን ትንሣኤ እና ሕይወት እርሱ መሆኑን በማሳየት የበለጠ አጽንቶታል። ኃይል እና ሥልጣኑን በይፋ አሳይቷልና።

## 3. በትንሣኤው መስቀል እና ሞት ትርጉማቸው ተለውጧል።

የእንጨት መስቀል በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ትምህርት ላይ እንደምናገኘው ሮማውያን እጅግ አደገኛ ወንጀለኞችን የሚቀጡበት አሰቃቂ የግድያ መሣርያ ነበር። ይህ መቅጫ እና መቀጣጫ የነበረው መስቀል በጌታችን ትንሣኤ ምክንያት የክርስቲያኖች መመኪያ፣ ጠላት ዲያብሎስን ማሳፈሪያ፣ የአምላክ ዙፋን፣ የነጻነት ቀንዲል፣ የአሸናፊነት ዓርማ ሆኗል። ሰይጣን ብዙ ጊዜ በጌታችን የተሸነፈ ቢሆንም በመስቀል የተሸነፋት ሽንፈት ግን ከሁሉ ትልቃለች። የጌታችን ትንሣኤ የሰይጣን እና ግብረ አበሮቹን ፍጹም ውድቀት ያሳየ ዐቢይ ኩነት ነው። ለዚህም ነው በዘመነ ትንሣኤ “አሰሮ ለሰይጣን አግዓዞ ለአዳም” ትርጉም “ሰይጣንን አሰረው አዳምን ነጻ አወጣው” እያልን ሰላምታ የምንለዋወጠው።

ከመስቀል ቀጥሎ ሌላው ትርጉሙ የተቀየረው ሞት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የኃለኛው ጠላት ብሎ የጠቀሰው ይህ ሞት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እጅግ አስከፊውና የመጨረሻው ጠላት ነው። (፩ኛ ቆሮ. ፲፭ ÷ ፳፮)

በቀደመው ዘመን የሰው ልጅ ሕይወት በኃጢአት ፍርድ ወይም ሞት ተጀምሮ ከዚያም ሞትን በማሰብ በጭንቅ እና በፍርኃት በመራራ ሕይወት ቀጥሎ ከዚያ ደግሞ በሞት (ርደተ መቃብር እና ርደተ ሲኦል) የሚፈጸም ሆኖ ነበር። እንግዲህ የጌታ ትንሣኤ በዚህ ክፉ ጠላት ላይ የተገኘ ድል ነው። ስለዚህም ነው የትንሣኤው ዘመን ደስታችን እጥፍ ድርብ የሚሆነው።

በብሉይ ኪዳን ሞት የዲያብሎስ እጅ ላይ የመውደቂያ መንገድ በመሆኑ ሙት አካል መንካት እንኳ መርከስ እስኪሆን ድረስ የሚጠላ እና የሚፈራ እንዲሁም እንደ ሄኖክ እና ኤልያስ ካሉት በቀር የማያመልጡት አስከፊ ፍጻሜ ነበር።

ምስጋና እና ክብር ለአምላካችን ይሁንና ከጌታ ትንሣኤ በኋላ ግን ሞት "ክርስቲያኖች የሚረግጡት፣ ጥርሱ የወለቀ፣ ኃይሉ የደከመ ያረጀ አንበሳ" ሆኗል። (ቅዱስ አትናቴዎስ)

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ሞትን እንዲህ እያለ ዘብቶበታል፤ "ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ ድል መንሣትህ የት አለ ?"(፩ኛ ቆሮ. ፲፭ ÷ ፶፭) አስቀድሞ ነቢያት እና አበው በታላቅ ጭንቀት የሚቀበሉት ሞት በዘመነ ሐዲስ ግን ሰማዕታት በታላቅ ደስታ እና ድፍረት የሚቀበሉት ጻድቃን በፈቃዳቸው በሕይወታቸው ላይ የሚያውጁት ማዕዶት( ፋሲካ) ሆኗል።

በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ጊዜ የሐዋርያት ደስታ እጅግ ልዩ ነበር። "ደቀ መዛሙርቱም ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው" (ዮሐ ፳፥፳) ጌታም በትንሣኤው ስለሚሆነው ደስታ አስቀድሞ ነበሯቸው ነበር። እንዲህ ሲል "እንደገና አያችኋለሁ ልባችሁም ደስ ይለዋል። ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም" (ዮሐ ፲፮ ÷ ፳፪) ይህ የነገራቸው ቃል መፈጸሙ በግብረ ሐዋርያት ላይ እንደሚከተለው ተዘግቦ ይገኛል። "ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግስት እየነገራቸው በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው" (ሐዋ ፩ ÷ ፫)

## በዘመነ ትንሣኤ ምን እናድርግ ?

እንግዲህ ከላይ እንደተመለከትነው ዘመነ ትንሣኤ የደስታ እና ጸጋ እግዚአብሔር የበዛበት ዘመን በመሆኑ ምክንያት መጾም እና መስገድ የለም። ደስታን እናደርግ ዘንድ እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህቺ ናትና ደስ ሊለን ይገባል። (መዝ ፻፲፯ ÷ ፳፬) በትንሣኤው የተገኘው ደስታ የነፍስም የሥጋም ነው። ማለትም ሥጋ ፈርሶ በስብሶ እንደማይቀር የተረጋገጠበት ነፍስም ከሲዖል ባርነት ነጻ የወጣችበት ነው። ይህም በመሆኑ ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ሥጋም ነፍስም በዘመነ ትንሣኤ ይደሰቱ ዘንድ ትፈቅዳለች። ይህ ሲባል ግን ሥጋችንን ከመጾም እና ከመስገድ አሳርፈን እንደምናለመልመው ሁሉ ነፍሳችንም በቃለ እግዚአብሔር ፣ በመዝሙር ምስጋና በቅዳሴ እና በምግባረ ሰናይ ልትለመልም ይገባል። የነፍሳችንን ትተን የሥጋችንን ደስታ ብቻ ከፈጸምን ግን የጌታችን ከሞት መነሣት ዓላማ አልገባንም ማለት ነው። የጌታችን ትንሣኤ ዓላማ እኛን ከኃጢአት ውድቀት ማንሣት እንጂ ወደ ኃጢአት ጉድጓድ መጣል አይደለም።

በዚህ በዘመነ ትንሣኤ ጾም እና ስግደት አለመኖሩ የ40 ቀን ጾሙን ድካም ለማካካስ ወይም ጾም እና ስግደት የማይገባ ስለሆነ አይደለም። በትንሣኤው ጸጋ እግዚአብሔር እንዴት እንደበዛች ለማሳየት ነው እንጂ ከዓመቱ ቀናት አብዛኛዎቹ የጾም ቀናት መሆናቸው የታወቀ ነው። ይህ መሆኑ ለኃጢአት ውድቀት ሳይሆን ለበለጠ መንፈሳዊ ብርታት እና ፍቅረ እግዚአብሔርን ለማስተዋል ሊሆን ይገባል። ስለዚህም ሊቃውንት አባቶቻችን እንደሚያስተምሩት ገበሬ በክረምት የዘራውን ዘር እና የለፋውን ልፋት ፍሬ በአጨዳ ጊዜ እንዲያገኝ እኛም በጾም ወቅት በሥጋችን ላይ የዘራነው ዘር እና የደከምነው ድካም ፍሬው በዘመነ ትንሣኤ ሊታይ ሊሰበሰብ ይገባል። ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "በመንፈስ ጀምራችሁ በሥጋ ትጨርሳላችሁን ?"( ገላ. ፫ ÷ ፫) ብሎ እንዳይወቅሰን በመንፈስ ልንመላለስ፣ ራሳችንን ከኃጢአት ርኩሰት ልንጠብቅ እንዲሁም በትንሣኤ ልቡና ለኋለኛው ትንሣኤ ልናዘጋጅ ይገባል።

ልዑል እግዚአብሔር አምላካችን ስለቸርነቱ ብዛት ከኃጢአት ርቀን፣ ተጠብቀን ንስሐ ገብተን ቅዱስ ቁርባን ተቀብለን የአዲሲቷ ሰማይ የአዲሲቷ ምድር ወራሾች እንሆን ዘንድ የእርሱ መልካም ፈቃድ ይሁንልን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል
ወለመስቀሉ ክቡር
አሜን።

# 3. ግብረ ማኅበረ ቅዱሳን

## ማኅበረ ቅዱሳን የአብነት ትምህርት ቤቶችን ከመደገፍ አንጻር ያደረገው አስተዋጽኦ

### 1. የአብነት ትምህርት ቤት ታሪክ

አብነት ማለት አባትነት ማለት ሲሆን በአብነት ትምህርት ውስጥ መምህሩ በእውቀት አርአያነት ለተማሪው ተማሪው ደግሞ በትሕትና አርአያነት ለጓደኞቹ እና በአካባቢው ለሚኖረው ማኅበረሰብ በሕይወቱ በማስተማር አብነት ይሆናል፡፡
የአብነት ትምህረት ጀማሪው እግዚአብሔር ሲሆን እርሱም አዳምን በቃል በማሰረዳት ጀምሮታል። በመቀጠልም ሙሴ በጽሑፍ ሲያጠናክረው ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም በተግባር አጽንቶታል፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአብነት ትምህርት ቤቶች የንባብ፣ የቅዳሴ፣ የዜማ፣ የአቋቋም፣ የቅኔ፣ የትርጓሜ መጻሕፍትና የቁጥር /አቡሻኽር/ ወዘተ ብለን የምንጠራቸው ትምህርቶች የሚሰጥባቸው የትምህርት ተቋማት ናቸው።

የአብነት ትምህርት ቤቶች ጥንታውያን ሁለገብ የእውቀት ማእከላት ሲሆኑ በተለይም ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ሰዎች ንባብ፣ ጽሑፍ፣ ሥዕል፣ ቅርጻ ቅርጽ፣ ምሕንድስና፣ ሕግ፣ አስተዳደር፣ ሕክምናና ሌሎች ጥበባትን የሚማሩት ከአብነት ት/ቤቶች ነበር፡፡

### 2. የአብነት ት/ቤቶች አስተዋጽኦ ለቤተ ክርስቲያን እና ለሀገር

#### 2.1 ለቤተ ክርስቲያን፡-

- ሃይማኖታዊ ትምህርት በማስፋፋት ዋነኛ ተዋናዮች ነበሩ፤ አሁንም ናቸው፡፡
- ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሳይፋለስና ሳይበረዝ እንዲተላለፍ በማድረግ አገልግለዋል፡፡ የካህናትና የሊቃነ ጳጳሳት መገኛ ምንጭ አብነት ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡

#### 2.2 ለሀገር ዕድገት፡-

- በትምህርትና በፍልስፍና፣ በአስተዳደር፣ በሕግ፣ ወዘተ መሠረት ጥለዋል፡፡
- የሥነ-ጥበብ እና የኪነ ሕንጻ ውጤቶች ዛሬም ድረስ የሀገሪቱ ዋነኛ የቱሪዝም መስህቦች በመሆን የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው፡፡
- እስከ 20ኛ መቶ ክፍለ ዘመን የሀገሪቱ የትምህርት ተቋም ነበሩ፡፡ ለሀገር፡ የትምህርት ሚኒስቴር ሳይኖር መሪ ሆነው አገልግለዋል፡፡
- በሀገራችን አንጋፋ የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች የአብነት ትምህርት በቶች ውጤቶች ሲሆኑ ንባብ፣ ዜማ፣ ቅኔ እና የመጻሕፍት ትርጓሜ የተማሩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ደብተራ ዘነበ፣ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወ/ሥላሴ፣ ቀኝ ጌታ ዮፍታኄ ንጉሤ፣ ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ፣ ተመስገን ገብሬ፣ ጸሐፊ ተውኔት መንግሥቱ ለማ፣ ብላቴን ጌታ ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን፣ ዮሐንስ አድማሱ የአብነት ትምህርት ቤት ካፈራቸው ታላላቅ የሀገር ባለውለታዎች ከሆኑት የጠቀስነው ጥቂቶቹን ነው፡፡

### 3. ማኅበረ ቅዱሳን የአብነት ትምህርት ቤቶችን ለመደገፍ መነሻ የሆኑ ምክንያቶች

ቤተ ክርስቲያን የገሃነም ደጆች የማያናውጧት ብትሆንም ሁሌም በፈተና ያለች በመሆኗ በውስጥ እና በውጪ ህልውናዋን የሚፈታተናትን ሁሉ በመቋቋም ረገድ ማኅበረ ቅዱሳን ነቅቶ እና ተግቶ እየሠራ ይገኛል፡፡ ገዳማት እና አድባራት በተለያየ ጊዜ ዘርፈ ብዙ ችግሮች የገጠሟቸው ሲሆን፣ ቀጥሎ ያሉትን ዋና ዋና ምክንያቶች መጥቀስ ይቻላል፡፡

- በመሬት ላራሹ አዋጅ ምክንያት አብዛኛው የአብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማት መሬት መወሰዱ ከዚያ በሚገኝ ምርት ይተዳደሩ የነበሩ መምህራን እና ተማሪዎች እንዲሰደዱ ማድረጉ፣
- የሀገሪቱ የኑሮ ውድነት እየተባባሰ መምጣቱ እና ከዚህም የተነሣ ተማሪዎች ከኅብረተሰቡ በእንተ ስማ ለማርያም ብለው ቁራሽ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ ድጋፍ ማግኘት አለመቻላቸው፣
- ለአብነት ትምህርቱ ያለው በጎ አመለካከት ወደ አሉታዊ መለወጥ፣
- የዘመናዊ ትምህርት መምጣት ከፈጠረው ተጽእኖ በተጨማሪ ተያይዞና ተቀናጅቶ አለማደግ፣
- የጉባኤ ቤቶች ወንበር መታጠፍ (በተለይም የንባብ፣ የዜማና የቅዳሴ)፣
- የመምህራን ወደ ከተማ መፍለስና ተተኪ የጉባኤ ቤት መምህር አለመኖር፣
- ለተሐድሶ መናፍቃን ሰለባ መሆን፣
- በአንድ ሙያ ላይ ማተኮር ሙሉውን ጉባኤ አለመማር፣
- መጽሐፈ መነኮሳትን የሚያስተምርና የሚማር መቀነስ፣
- የሊቃውንት ጉባኤ በተወሰኑ ቦታዎች ቢኖርም በስፋት አለመሰጠት፣
- ዐይናማ መምህራንን የሚተካቸው መጥፋት ወዘተ... ዋናዎቹ ናቸው፡፡

### 4. ማኅበረ ቅዱሳን አብነት ትምህርት ቤቶችን ለመደገፍ ያከናወናቸው ሥራዎች

#### 4.1. ወርኃዊ የገንዘብ ድጎማ

ማኅበረ ቅዱሳን የአብነት ትምህርት ቤቶች ላይ የሚደርሰውን ችግር ለመቀነስ ታሳቢ ያደረገ በ1998 ዓ.ም "የአብነት ትምህርት ቤቶች መርጃና ማቋቋሚያ" የሚል መርሐ ግብር ቀርጾ ላለፉት ዓመታት በበርካታ አብነት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ መምህራን እና ተማሪዎች ከ33 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አድርጓል፡፡

#### 4.2. የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ነጻ የትምህርት ዕድል

የአባ ዮርጊስ ዘጋስጫ ነጻ የትምህርት ዕድል በመንፈሳዊ እና በዘመናዊ ትምህርት የተሻሉ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ለማፍራት በ2007 ዓ.ም የተጀመረ መርሐ ግብር ሲሆን ከተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ጀምሮ በማስተማር በርካታ የአብነት ተማሪዎች የዕድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስችሏል፡፡

ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ በተደራጀ እና በተጠናከረ መልኩ በሦስት ዘርፎች በመክፈል ማለትም ከአብነት ወደ ዘመናዊ፣ ከዘመናዊ ወደ አብነት እንዲሁም መንፈሳዊ ኮሌጅ ላይ የነጻ ትምህርት ዕድል በመስጠት በተግባር ተኮር 950፣ ከዘመናዊ ወደ አብነት 7፣ ከአብነት ወደ ዘመናዊ 45 እና በመንፈሳዊ ኮሌጅ 67 መምህራንን ማስመረቅ የተቻለ ሲሆን ለዚህም ከ5 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጓል፡፡

በ2016 ዓ.ም በሦስቱም ዘርፍ ለ67 የዕድሉ ተጠቃሚዎች ከ1.4 ሚሊዮን ብር በላይ ዕቅድ ይዞ ክፍያ እየፈጸመ እና እያስተማረ ይገኛል።

### 4.3. የአብነት ትምህርት ቤቶች ሥልጠና

የአብነት ተማሪዎች ከአብነት ትምህርቱ ጎን ለጎን መሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርት ዕውቀት እንዲኖራቸዉና ከውስጡ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በተጨማሪ በውጭ አገልግሎትም እንዲሳተፉ ለማስቻል ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ ከ 3 ሺህ በላይ ተማሪዎችን ማሠልጠን ተችሏል። ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ የሚሰጡ ሥልጠናዎችን በደረጃ በመክፈል ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ ሦስት ለአብነት ተማሪዎች ዐቅም ሊያሳድጉ የሚችሉ ሥልጠናዎችን ከ6 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ተማሪዎች ሰጥቷል።

### 4.4. ጊዜያዊ ድጋፍ

ለአብነት ትምህርት ቤቶች ከድጎማ ድጋፍ በተጨማሪ በተፈጥሮ እና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ምክንያት የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዳያቋረጥ በርካታ ድጋፎች ሲያደርግ ቆይቷል አሁንም በማድረግ ላይ ይገኛል።

### 4.5. የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች

- **74 የገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶች ተሠርተዋል፡፡**

  የአብነት ትምህርት ቤቶች በራሳቸው ዐቅም በገቢ ራሳቸዉን ችለው የመማር ማስተማር ሥራቸውን እንዲያከናውኑ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ማለትም የገቢ ማስገኛ ሕንፃዎች፣የአትክልትና መስኖ ልማት፣የንብ ማነብ ሥራዎች፣የወተት ላም ፕሮጀክት ፣ወፍጮ፣ከብት ማድለብ፣ሽመና ሥራዎች እንዲሁም ሌሎች ተሠርተዋል። በዚህም መሠረት የአብነት ትምህርት ቤቶች ለቀለብ ፍለጋ የሚያባክኑትን ጊዜ በበርካታ አካባቢዎች ማስቀረት ተችሏል።

- **86 የአብነት ትምህርት ጉባኤ ቤት እና ሌሎች ግንባታዎች ተሠርተዋል።**

  የአብነት ትምህርት ባልተስፋፋባቸው አካባቢዎች የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት የአካባቢውን ቋንቋ በሚችሉ አገልጋዮች ለማሟላት በማሰብ ሙሉ ጉባኤ ቤት ማለትም፡- ደረጃን የጠበቀ የተማሪዎች ማደሪያ ፣የመምህራን መኖሪያ፣ የመማሪያ ጉባኤ ቤት፣ማብሰያ፣ ሻወር እና ሽንት ቤት የተሟላላቸው ፕሮጀክቶች በበርካታ አህጉረ ስብከቶች ተገንብተዋል፤አሁንም በመገንባት ላይ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ የአብነት ትምህርት ቤቶች የማጠናከሪያ ሥራዎች እና የሥልጠና ማእከል ግንባታዎች ተሠርተዋል።

**5. ማኅበሩ የአብነት ትምህርት ቤቶች ዙርያ በሠራቸው ሥራዎች የመጡ ለውጦች**

- ድጎማ በሚያገኙ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ቁጥር እንዲጨምር አስችሏል፤
- በአካባቢው ቋንቋ ማገልገል የሚችሉ ያስመሰከሩ መምህራንን ማፍራት ተችሏል፤
- የአብነት ትምህርት በሌለባቸው አካባቢዎች የአብነት ትምህርት ቤቶችን በመመሥረት አገልጋይ ማፍራት ተችሏል፤
- በመጥፋት ላይ የነበሩ ጉባኤ ቤቶች(አቡሻኽር፣ ቆሜ፣ ሰለልኩላ፣ አጫበር) ሙሉ በሙሉ እንዳይጠፉ ማዳን ተችሏል፤
- በመጻሕፍት ትምህርት ቤቶች ገብተው የሚማሩ ተማሪዎችን ቁጥር መጨምር ተችሏል፤
- ከ"የቆሎ ትምህርት ቤት" እና "የቆሎ ተማሪ" ከሚለው አጠራር የአብነት ት/ቤት እና የአብነት ተማሪ ወደሚል አጠራር ለመቀየር ተችሏል፤
- በሁለንተናዊ መልኩ ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል የሚችሉ ተተኪ ሊቃውንትን ማፍራት ተችሏል፤
- ምቹ እና የተሻለ የመማሪያ ጉባኤ ቤት እንዲኖር አስችሏል፤
- ለምእመናን በግልም ሆነ በማኅበር በመሰባሰብ ገዳማትን እና የአብነት ትምህርት ቤቶችን መርዳት የሚያስችላቸውን ግንዛቤ ፈጥሯል፤
- የወቅቱን የቤተ ክርስቲያን ችግሮች የተረዱ እና በተለያየ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ውሰጥ ገብተው እያገለገሉ ያሉ መምህራንን ማፍራት ተችሏል፤

**6. ማኅበረ ቅዱሳን የአብነት ትምህርት ቤቶችን ከመደገፍ አንጻር ያጋጠሙት ችግሮች**

ማኅበረ ቅዱሳን ቤተ ክርስቲያን በተፈተነችበት ጊዜ እና ቦታ ሁሉ በመገኘት የልጅነት ግዴታውን በመወጣት ላይ ሲሆን፣ የአብነት ት/ቤቶችን ከመደገፍ አንጻር ከገጠሙት ተግዳሮቶች ጥቂቶች የሚከተሉት ናቸው:-

- በአብዛኛው የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ላይ የአብነት ትምህርት ቤቶችን ስለመደገፍ የላቀ ግንዛቤ አለመኖር፣ ለመደገፍም ፍላጎት ያለመኖር፣
- የአብነት ት/ቤቶች መምህራንና ተማሪዎች አመለካከትና የአስተሳሰብ ለውጥ በተፈለገው ልክ አለመሆን፣
- በቂ ድጋፍ በተፈለገዉ ጊዜ ከድጋፍ አድራጊዎች አለማግኘት፣
- ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቁ፣ ዘመኑን የዋጀና ተግዳሮቶችን ተቋቁሞ ማገልገል የሚችል አገልጋይ በሚፈለገው ልክ አለማፍራት፣
- የተደራጀ የአብነት ት/ቤቶች መምህራንና ደቀ መዛሙርት መረጃ አለመኖር፣
- በየጊዜው የሚከሠቱ ሰው ሠራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎች ድጋፎችን በተፈለገው ጊዜ ተደራሽ ለማድረግ መሰናክል መሆን የሚሉትን ከብዙ በጥቂቱ መጠቀስ ይቻላል፡፡

## 7. ማኅበሩ በአብነት ት/ቤቶች ዙሪያ ወደፊት ያለበት ሥራዎች

በ5ኛው የማኅበረ ቅዱሳን ስልታዊ ዕቅድ ትኩረት ሰጥቶ የሚሠራቸው በርካታ ተግባራት አሉት። ከእነዚህም መካከል፡- የገዳማት እና የአብነት ትምህርት ቤቶች ልህቀት ማእከላትን ማቋቋም፣

- በአብነት ትምህርት ቤቶች እና ገዳማት ላይ የዐቅም ማሳደጊያ ሥራዎችን መሥራት፣
- የአብነት ትምህርት ቤቶች ባልተስፋፉባቸው አካባቢዎች የአብነት ትምህርት ቤቶችን መመሥረት፣
- ለአብነት ትምህርት ቤቶች የድጎማ ድጋፍ ማድረግ፣
- ለአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ነጻ የትምህርት ዕድል ተጠቃሚዎች ድጋፍ ማድረግ፣
- በወቅታዊ ጉዳይ ችግር ለገጠማቸዉ ገዳማት እና የአብነት ትምህርት ቤቶች ጊዜያዊ ድጋፍ ማድረግ፣

## 8. በ2016 ዓ.ም በማኅበረ ቅዱሳን እየተሠሩ ያሉ ፕሮጀክቶች

በ2016 ዓ.ም በገዳማት እና የአብነት ትምህርት ቤቶች እየተተገበሩ/እየተሠሩ ያሉ ፕሮጀክቶች ከዚህ በታች በሠንጠረዡ ተዘርዝረዋል።

| ተ/ቁ | የፕሮጀክቱ ስም | አጠቃላይ የሚያስፈልግ በጀት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | ምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት የአብነት ትምህርት ቤት ማቋቋሚያ ፕሮጀክትየፕሮጀክቱ ስም | 8,709,353.07 ብር | |
| 2 | የደብረ ሐዊ ቅዱስ ያሬድ አንድነት ገዳም ሁለገብ ሕንጻ ግንባታ ፕሮጀክት | 47,467,150.28 ብር | |
| 3 | የመነከሳት፣ የአብነት መምህራን እና ደቀመዛሙርት ሁለንተናዊ ዐቅም ማሳደጊያ ሥልጠና ፕሮጀክት | 1,765,000.00 ብር | |
| 4 | የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ነጻ የትምህርት ዕድል ፕሮጀክት | 1,741,000.00 ብር | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5 | የአብነት ትምህርት ቤቶች ድጎማ ፕሮጀክት | 13,391,310.00 ብር | |
| 6 | በወቅታዊ ጉዳዮች ጉዳት ለደረሰባቸው ገዳማትና አብነት ት/ቤቶች አስቸኳይ ድጋፍ | 5,285,441.4 ብር | |
| 7 | የበደሌ የገቢ ማስገኛ ፕሮጀክት | 26,429,300.00 ብር | |
| 8 | ሐዋርያዊ ተልእኮ በሚተገበርባቸው አካባቢዎች ካህናትን የማፍራት ፕሮጀክት | 1,750,000.00 ብር | |
| | አጠቃላይ ድምር | 106,538,554.75 ብር | |

**9. ከምእመናን ምን ይጠበቃል?**

በማኅበረ ቅዱሳን በቅዱሳት መካናት እና መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች አገልግሎት ማስተባበሪያ የሚከናወኑ ተግባራት ብዙ የገንዘብ ድጋፍ የሚጠይቁ ናቸው። ስለዚህ የተለያዩ ማኅበራት ብሎም እያንዳንዱ ምእመን ለገዳማት እና የአብነት ትምህርት ቤቶች ለአጭር እና ለረዥም ጊዜ የድጋፍ ዕቅድ በመያዝ ማገዝ ይጠበቅባቸዋል። በተለይ ደግሞ እየተተገበሩ ላሉ ፕሮጀክቶች፣ ለገዳማት እና አብነት ትምህርት ቤቶች ወቅታዊ ድጋፍ፣ የአብነት መምህራንና የአብነት ተማሪዎች ሥልጠና እንዲሁም ለአብነት መምህራንና ተማሪዎች ድጎማ ጊዜ የማይሰጡ እና የሁሉንም ርብርብ የሚጠይቁ በመሆናቸው ምእመናን የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ ይገባል።

**ማጠቃለያ**

ማኅበረ ቅዱሳን በአጠቃላይ እነዚህን ፕሮጀክቶች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ አገልግሎቷን እንድትወጣ የሚኖራቸው ሚና የጎላ በመሆኑ ከድጋፍ አድራጊዎች ገንዘብ የማሰባሰብ ሥራ በማከናወን ላይ ይገኛል። በመሆኑም ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው ጊዜ መጠናቀቅ እንዲችሉ ድጋፋችንን አጠናክረን መቀጠል ይገባናል።

# 4. የአኀት አቢያተ ክርስቲያናት ተሞክሮ ዳሰሳ

**በኑሮ ራስን መቻል ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ያለው ጠቀሜታ ከሕንድ የማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተሞክሮ አንጻር**

**መግቢያ**

የሰው ልጅ በዚህች ምድር ላይ ሲመላለስ "በላብህ ወዝ ጥረህ ግረህ ብላ" የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ መፈጸምና ከአገኘውም ላይ ለሌላቸው ማካፈል እንደሚገባው ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል፡፡
በዚህ መነሻነት አንድ ክርስቲያን ሆነ ቤተሰቡ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን የተለያየ መዋቅር ውስጥ በየመዓርጋቸው የሚያገለግሉ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሰው በምድር ሲኖር ተግቶ መሥራት እንዳለበት ማስተማር፣ መምከር፣ አቅጣጫ ማሳየት እንዲሁም አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ሁሉ ክርስቲያኖችን መደገፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ለዚህም ጥሩ መሳያ የምትሆነን በሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ ስብከት ላይ የተመሠረተችው የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስትሆን ከታሪኳ በመነሣት በምጣኔ ሀብት ልጆቿን እንዴት አስተባብራ እየሠራች እንደሆነ፣ ያሏት ልማት ተቋማት፣ ያገኘችው ጥቅም እና ልጆቿ በመንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ ያላቸውን ሱታፌ በተወሰነ መልኩ እንመለከታለን፡፡

**የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ማን ናት?**

የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ናት፤ የተመሠረተችውም ከጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ በሆነው በቅዱስ ቶማስ ስብከት ሲሆን፣ ሐዋርያው በሕንድ ደቡባዊ ምዕራብ የኬርላ ግዛት የባሕር ዳርቻ እ.ኤ.አ በ52 ዓ/ም እንደ መጣ ይነገራል፡፡ የሕንድ ኦርቶዶክስ ምእመናን ቁጥር ከአጠቃላይ የሕንድ ሕዝብ አንጻር ከ 3% (2.5 ሚሊዮን ) በታች ሲሆን በደቡባዊ ሕንድ የሚገኘው የኬርላ ግዛት ከአጠቃላይ የሀገሪቱ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ውስጥ 28% ይይዛል፡፡ በኬርላ ግዛት የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ቁጥር ከካቶሊክ እምነት ተከታዮች በመቀጠል ሁለተኛውን ቁጥር ይይዛል፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ የሕንድን መሬት በረገጠበት የማላባር የባሕር ዳርቻ የመጀመሪያውን ቤተ ክርስቲያን መሥርቷል። በመቀጠልም በተለያዩ የደቡባዊ ሕንድ ግዛቶች በመዟዟር ክርስትናን ያስፋፋ ሲሆን በአጠቃላይ ስምንት አብያተ ክርስቲያናትን በእመቤታችን ስም መሥርቷል፡፡ ቅዱሱ የማላባር (Malabar) እና የደቡብ ሕንድ ሐዋርያ ብቻ ሳይሆን ለመላዋ ሕንድ ብሎም ለእስያ ሐዋርያ ነበር።

በኋላም ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አንሥቶ የሕንድ ቤተ ክርስቲያን ከፐርሽያ (የአሁኖቹ ኢራቅ እና ኢራን) ጋር የቀረበ ግንኙነት ማድረግ ጀመረች፡፡ የሕንድ ቤተክርስቲያን ከፐርሽያኖች የምሥራቅ ሶርያን ቋንቋ እና የአምልኮ ሥርዓቶችን በመውረስ በሂደት የሶርያ ክርስቲያኖች ለመባል ችለዋል። የሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዓለም የክርስቲያኖች ታሪክ ውስጥ በጥንታዊነት የምትታወቅ እና በሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ የተመሠረተች ሐዋርያዊት ናት።

በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በእስልምና መነሣትና የሕንድ የባሕር ዳርቻ አካባቢዎች በሙስሊሞች መወረር ምክንያት የሕንድ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች የክርስቲያን ሀገሮች ተነጥላ (ተገልላ) ለመቆየት ተገዳለች። ይሁንና ያሉትን አማራጮች በሙሉ በመጠቀም የነበረውን ሐዋርያዊ ትውፊት ተከትለው ጳጳሳትን ከምዕራብ እስያ ለማግኘት ጥረት ያደርጉ ነበር።

የማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከምሥረታዋ ጀምሮ እ.ኤ.አ እስከ 1657 ድረስ አንድነት ያላት እና የራሷን አገር በቀል ማንነት አስጠብቃ ለመቆየት ከፍተኛ ጥረት እና ተጋድሎ ስታካሄድ የነበረች ናት።

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሮማን ካቶሊኮች እና በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ፕሮቴስታንቶች ወደ ሕንድ እስኪ መጡ ድረስ ብቸኛዋ ቤተ ክርስቲያን ነበረች፡፡

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፖርቹጋል ቅኝ ገዢዎች በመታገዝ የሮማን ካቶሊክ ከማላንካራ ቤተ ክርስቲያን ጋር ግንኙነት በመፍጠር በረጅም ሂደት እና መስተጋብር፣ የሮማን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በኃይል በማላንካራ ክርስቲያኖች ላይ የበላይ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል።

ይህንን በቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰውን ፈተና ለመቀልበስ እ.ኤ.አ በ1653 በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የማላንካራ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች በጋራ ሆነው ኮቺን አካባቢ ማታንቼሪ (Mattancherry) በተባለ ቤተ ክርስቲያን፣ መስቀል ቆሞበት በነበረው ስፍራ በመሰባሰብ በመስቀሉ ላይ ገመድ በማሰርና እየአንዳንዱ የተሰበሰበ ክርስቲያን ገመዱን በመያዝ (በመንካት) ከሮማ ካቶሊክ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ላይኖራቸው በመማማል፣ በኃይል ከተጫናባቸው የሮም ካቶሊክ አስተምህሮ በመላቀቅ የኦሬንታል ቤተ ክርስቲያን መገለጫዎችን እና ሀገር በቀል ትውፊቶቻቸውን እንደገና በማደስ ወደ ቀደመ ማንነታቸው ተመልሰዋል። ይህንን የማላንካራውያንን አንድነታቸውን ያልተቀበለችው የሮማን ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ከቅኝ ገዢዎች ባላት ድጋፍ ከፍተኛ ኃይልን በመጠቀም በወሰደችው እርምጃ ከማላንካራ ክርስቲያኖች ጥቂት የማይባሉ የሮም ካቶሊክን በኃይል እንዲቀላቀሉ በማድረግ በሂደት የካቶሊክ ተከታዮች በክርስቲያኖቹ ላይ በቁጥር የበላይ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል።

ከዓመታት በኋላ በብዙ መከራ እና ትግል በኋላ ከሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በተቃራኒ የቆሙት ኦርቶዶክሳውያን ራሳቸውን ነጻ ለማውጣት ከምዕራብ ሶርያ በሚላክ ጳጳስ እየተመሩ ቀጠሉ፡፡ ይህ ዓይነት ግንኙነት እ.ኤ.አ ከ1665 የጀመረው የፖለቲካው ርእዮተ ዓለም መቀየርና ፖርቹጋሎች ከደቡባዊ ሕንድ ተባረው የፕሮቴስታንታዊ መንፈስ የነበራቸው ደቾች (Dutch) ሲተኳቸው ነበር፡፡ ራሳቸውን ከሮማ ካቶሊክ ነጻ ያደረጉት የማላንካራ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች እ.ኤ.አ እስከ 1816 ድረስ በራሳቸው የሕንድ ጳጳሳት እየተመሩ ማርቶማ (Mar Thoma) በሚል ስያሜ እየተጠሩ ቀጥለዋል።

በኋላ ይህቺ ቤተ ክርስቲያን የምትሾማቸውን ጳጳሳት (ሜትሮፓሊታኖች) ማርዲዮናሲዮስ (Mar Dionysius) በማለት ቀጥላ ዛሬ ላይ የሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን “The Indian Orthodox Church” ተብላ ለመጠራት ችላለች፡፡

ማላንካራ የሚለው ቃልም የመጣው ማሊአንካራ (Maliankara) ከሚለው ጥንታዊ የከሬላ (ማላባር) የባሕር ዳርቻ ስም ሲሆን ይህ ቦታ ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ ለመጀመርያ ጊዜ የሕንድን መሬት የረገጠበት እና የምሥራቹን ወንጌል የሰበከበት ቦታ ነው፡፡

የማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን በሕንድ ሀገር ራሷን ችላ ነጻ በሆነ ሁኔታ የምትተዳደርና (autonomous and autocephalous) መንበረ ፓትርያርኳ (Headquarters) በደቡባዊው የከሬላ ግዛት ኮታይም ከተማ የሚገኝ ነው፡፡

የሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በመላው ዓለም የሚገኙ 30 አህጉረ ስብከት (dioceses) እና 33 ጳጳሳት ያሏት ሲሆን በውጭ የሚገኙ የቤተ ክርስቲያኗ ልጆች መንፈሳዊ ጉባኤያትን በማካሄድና ቤተ ክርስቲያን በመሥራት አስደማሚ የልማት ሥራዎችን በማከናወን የሕንድ ቤተ ክርስቲያን በልጆቿ አማካይነት ዓለም አቀፋዊ ማነነት እንዲኖራት አድርገዋል፡፡

የማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የምትከተለው ግልጽ የሆነ አሠራር ከሌሎች አኀት አብያተ ክርስቲያናት ለየት የሚያደርጋት ሲሆን፤ ታላቁ የማላንካራ ሲሪያን ክርስቲያን ማኅበር (በዓለም ላይ ታላቁ የቤተ ክርስትያን ፓርላማ ተብሎ የሚጠራው) የካህናትና የምእመናን ተወካዮችን ከዓለም ዙርያ የያዘ ሲሆን በየጊዜው የሚሰበሰብና ፓትርያርኩን ጨምሮ ጳጳሳትን እና የተለያዩ የቤተ ክርስቲያኒቱን ቁልፍ ቦታዎች የሚመሩ አካላትን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚመርጥ የክርስቲያኖች ስብስብ ነው፡፡

የማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በቀኖና ሁለት ሕንዳውያን አባቶችን ቅዱስ ብላ የሰየመች ሲሆን፣ የመጀመሪያው አባት ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘፐሩማላ (St. Gregorios of Parumala) እ.ኤ.አ በ1947 ሲሆን ሁለተኛው በ2003 እ.ኤ.አ ቅዱስ ጊዮርጊስ ዲዮናስዮስ (St. Geevarghese Dionysius) ነው።

የማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ኅብረትን ከመሠረቱት መካከል አንዷ ስትሆን ለሀገራዊ የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት መመሥረትም የጎላ ሚና ተጫውታለች፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ የተለያዩ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ልማታዊ እንቅስቃሴዎች በቁርጥ ቀን ልጆቿ የጎላ ሚና ያበረከተች እና በማበርከት ተከብራና ተሰሚ ሆና ዘመኑን ዋጅታ ወደ ፊት በመጓዝ ላይ ትገኛለች፡፡

**ይህ የመከራ ዘመን የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ምን አስተማራት?**

በእነዚህ የመከራ ዘመናት የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ልጆች የሆኑና ነገን አርቀው ማሰብ በቻሉ ባለ ራእዮች አማካይነት የተለያዩ አደረጃጀቶች በመፍጠር እና አስፈላጊውን ቅርብ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ዛሬ ለብዙዎች ምሳሌ የሆኑ መልካም ሥራዎችን እየሠሩ ይገኛሉ፡፡

በብዙ መከራና ፈተና ውስጥ ያለፉት የማላንካራ ኦርቶዶክስ ሲሪያን ቤተ ክርስቲያን ልጆች ይህን ድንቅ ሥራ የሠሩት፣ ነገን ማየት በቻሉ አባቶቻቸው እየተመሩ ሲሆን ዘመኑን ለመዋጀትም ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን እየሠሩ ይገኛሉ፡፡

የእኛም ቤተ ክርስቲያን በዘመናችን ለብዙ ውስጣዊ እና ውጫዊ ፈተና ተጋላጭ ሆናለች፡፡ በዚህም ምክንያት ካህናትና ምእመናን ለሞትና ለስደት ሲዳረጉ አብያተ ክርስቲያናት በየቦታው በእሳት እየተቃጠሉ ይገኛሉ፡፡ ትናንትና የነበሩ አባቶቻችን በዘመናቸው ለአጋጠሟቸው ፈተናዎች መፍትሔ እየፈለጉ እና የመፍትሔው አካል እየሆኑ ዛሬን እንዳስረከቡን ሁሉ፣ እኛም በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች ዘመናችንን ለመዋጀት እና ከማላንካራ ኦርቶዶክሳውያን የአገልግሎት አደረጃጀት መልካም ታሪክና ተሞክሮ ወስደን በግልና በጋራ የመፍትሔው አካል እንሆን ዘንድ ግድ ይለናል፡፡ ለዚህም የማላንካራ ቤተ ክርስቲያን ከሕፃናት ጀምሮ ሁሉም ምእመን በአገልግሎት መሳተፍ እንዲችሉ ከተመሠረቱት አደረጃጀቶች የተወሰኑትን ለትምህርት ይሆኑን ዘንድ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**1. የሰው ኃይል ማጎልበቻ ሚኒስትር** (Ministry of Human Empowerment)

የሰው ኃይል ማጎልበቻ ሚኒስትር የማላንካራ ኦርቶዶክስ ሲሪያን ቤተ ክርስቲያን ካሏት የአገልግሎት ክፍሎች መካከል አንዱ ነው፡፡ የሚኒስትሩ ዋና ዓላማ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን የቤተ ክርስቲያኗን የሰው ኃይል ዓቅም የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም መለየት፣ መግለጥ እና ማብቃት ነው፡፡ የሚኒስትሩ ሌላው ዓላማ የቤተሰብን ዓቅም ማጎልበት(Family Empowerment) ነው፡፡

**2. የምእመናን መንፈሳዊ ትምህርት መርሐ ግብር** (Theological Education Programmed for the Laity)

የዚህ ማኅበር ዋና ዓላማ ምእመናን መንፈሳዊ ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ መርሐ ግብሩ ሰዎችን ቀድሞ በማዘጋጀት የዘመኑን ተግዳሮት፣ የጊዜውን አስተሳሰብና ችግሮችን እንዲጋፈጡ በጥልቅ እምነት እና በክርስቲያናዊ እሳቤ ምላሽ እንዲሰጡ ማስቻል ነው፡፡ በተጨማሪም በዓለማዊ ሥራ ውስጥ ያሉ መሪዎች በቤተ ክርስቲያኗ መዋቅሮች ባሉ መንፈሳዊ ተቋማት ውስጥ ገብተው እንዲሠሩ ያበረታታል፡፡ መርሐ ግብሩ ወላጆች ልጆቻቸውን በትክክል እየተንከባከቡ እና እውነተኛ የክርስትናን መንገድ እያሳዩ እንዲያሳድጓቸውም ድጋፍ ያደርጋል፡፡

**3. የማላንካራ የሁሉም ሕፃናት ማኅበር**

ማኅበሩ የማላንካራ ኦርቶዶክስ ሲሪያን ቤተ ክርስቲያን የተማሪዎች ክፍል (Student Portion) ነው፡፡ ማኅበሩ በቤተ ክርስቲያን ያሉ ወጣቶች የተቀናጀ እድገት (integrated Personal development) ላይ የሚሠራ ነው፡፡ ዋናው ዓላማውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሁሉም ወንዶች እና ልጃገረዶች በአግባቡ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ፣ እንዲማሩ እና በጎ ሕይወት (Worship, Study and Virtuous life) እንዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡

**4. የቅዱስ ቶማስ የኦርቶዶክስ ካህናት ኅብረት**

የዚህ ኅብረት ዋናው ዓላማ ካህናት በጋራ የሚገኙበትን መድረክ በማዘጋጀት እርስ በእርስ ሐሳብ እንዲለዋወጡ፣ ለቅዱስ ሲኖዶስ ግብዓት የሚሆኑ ሐሳቦችን እንዲያቀርቡ፣ ስለራሳቸው እና አጠቃላይ ስለ ምእመናን ደኅንነት እንዲመክሩ የሚያደርግ ማኅበር ነው፡፡

**5. የሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሴቶች ኅብረት**

ይህ “ማርታ ማርያም የሴቶች ኅብረት” በሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥር ያለ የሴቶች ስብስብ ማኅበር ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያኗ ካሏት ትልልቅ መንፈሳዊ ማኅበራት አንዱ ሲሆን፣ ሁሉንም የቤተ ክርስቲያኗን ሴት ምእመናት ማኅበሩ በአባልነት የያዘ ነው፡፡ የማላንካራ ኦርቶዶክስ ሲሪያን ቤተ ክርስቲያን በዓለም ላይ ባሏት 30 አህጉረ ስብከቶች ባሉ አጥቢያዎች አደረጃጀት ፈጥሮ በአጥቢያ ላሉ ሴቶች በጋራ የሚያገለግል ስብስብ ነው፡፡ ማኅበሩ እ.ኤ.አ 1928 ሲመሠረት ዋናው ዓላማ የሴቶችን እና የቤተሰባቸውን መንፈሳዊ ሕይወት መከታተል፣ መደገፍ፣ በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማስቻል ነው።

### 6. የማር ጎርጎርዮስ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ተማሪዎች እንቅስቃሴ ኅብረት

የማር ጎርጎርዮስ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ተማሪዎች እንቅስቃሴ ኅብረት የማላንካራ ኦርቶዶክስ ሲሪያን ቤተ ክርስቲያን የተማሪዎች ክንፍ ነው፡፡ ከዛሬ መቶ ዐሥር ዓመት በፊት በማድራስ ግዛት ቸናይ (Madras-Chennai) ከተማ የሚገኙ ጥቂት የቤተ ክርስቲያን ተማሪዎችና መሪዎች በጋራ ሆነው በተለያዩ ኮሌጆች እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ክርስቲያን ተማሪዎች ጥልቅ የመንፈሳዊ ሕይወት እንዲኖራቸውና በትምህርታቸውም ንቁ እንዲሆኑ ለማድረግ በጋራ ማሰባሰብ እንደሚያስፈልግ ተገነዘቡ፡፡ በዚህ መነሻነት እ.ኤ.አ በ1907 የሲሪያን ክርስቲያን ተማሪዎች ስብስብ በሚል ማኅበር መሠረቱ፡፡

ይህ የሲሪያን ተማሪዎች ኮንፍረንስ እ.ኤ.አ በ1960 የአሁኑን ስም የማር ጎርጎርዮስ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ተማሪዎች እንቅስቃሴ ኅብረት እንዲያገኝ ተደረገ፡፡ ይህ ማኅበር በሕንድ ውስጥ ያለ የመጀመሪያው ትልቅ ዕድሜ ያለው የክርስቲያን ተማሪዎች ማኅበር ሲሆን፣ መሪ ቃሉም ማምለክ (Worship) ፣ማገልገል (Service) እና መማር (Study) የሚል ነው።

የማር ጎርጎርዮስ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ተማሪዎች እንቅስቃሴ ኅብረት ለረጅም ዓመታት በትምህርቱ ዘርፍ መልካም ሥነ ምግባራዊ (inter disciplinary) ግንኙነቶችን በማስጠበቅ እና የተለያዩ ዘርፎችን በመፍጠር እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡
በዚህ መሠረት፡-

- የኮሌጅ ተማሪዎች ኅብረት(College Students wing)
- የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ክንፍ (High School Students wing)
- የዩኒቨርስቲ አስተማሪዎች ኅብረት (University teachers association)
- የደረጃ መምህራን ኅብረት (School teachers association)
- የሕክምና ረዳቶች ስብስብ (Medical Auxiliary)
- የባለሙያዎች ስብስብ (Technical Auxiliary)
- የሰባክያን ስብስብ (Missionary forum)
- የሥነ ጽሑፍ ስብስብ (Literary forum)
- የኅትመት ክንፍ (Publication wing) እና ሌሎችም የአገልግሎትና የሥራ አደረጃጀቶች አሉት።

### 7. የኦርቶዶክስ ክርስቲያን የወጣቶች እንቅስቃሴ

ይህ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ወጣቶች እንቅስቃሴ የማላንካራ ኦርቶዶክስ ሴሪያን ቤተ ክርስቲያን የወጣቶች ክንፍ ሲሆን፣ በቤተ ክርስቲያንና በማኅበረሰቡ ባለው የነቃ አመራርና ክርስቲያናዊ ሕይወት የተመሰከረለት የ90 ዓመት ዕድሜ ያለው ማኅበር ነው፡፡

እ.ኤ.አ በ1933 አርቆ አሳቢው መሪ (Joseph Mar Severios) ፕሬዝዳንትነት እና ቄስ አብርሃም (Rev Fr Ts Abraham) ጸሐፊነት በአንድ አካባቢ ያሉ ወጣት ተማሪዎችን በጋራ በመሰብሰብ በአጥቢያ ደረጃ የሲሪያን ወጣቶች ሊግ በሚል እንዲደራጁ አደረጉ፡፡ ኅብረቱ ለቤተ ክርስቲያን እና ለማኅበረሰቡ እድገትና መልካምነት በሦስት ትልልቅ ዘርፎች፣ ማምለክ (worship) ፣ትምህርት (study) እና ማገልገል (service) ላይ ተሰማርቶ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡

የኅብረቱ የዘመናት እንቅስቃሴ ሥር የያዘው በቤተ ክርስቲያኗ በነበሩ ርእይ (Visionary) ባላቸው መሪዎች በ19ኛው መ.ክ.ዘ አጋማሽ ላይ ነበር፡፡ ይህ መንፈሳዊ ማኅበር የወጣቶች ስብስብ (Yuvajana Sangam) በሚል በተለያዩ ቦታዎች እና አጥቢያዎች ከሌሎች ማኅበራት (ሰንበት ትምህርት ቤቶች፣ ከማር ጎርጎርዮስ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ተማሪዎች እንቅስቃሴ ኅብረት፣ ከወንጌል አስተማሪዎች ወዘተ) ጋር በመሆን ውጤታማ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል፡፡

የማላንካራ ቤተ ክርስቲያን በተሃድሶ ቡድኖች በከፍተኛ ማዕበል ውስጥ በነበረችበት ዘመን፣ እናት ቤተ ክርስቲያን ችግሮችን እንድትሻገር ይህ የወጣቶች ኅብረት ከፍተኛውን ሚና ተጫውቷል፡፡

እ.ኤ.አ 1936 የተካሄደው ታሪካዊ ኮንፈረንስ የቤተ ክርስቲያኗን የወጣቶች ሊግ ርእይን በማስፋት እውቅና ያለው የቤተ ክርስቲያኗ የወጣቶች ክንፍ እንዲሆን በመወሰን እና እንዲጠናከር ሊቀ ጳጳስ (Metropolitan Geeverghese mar Philexinos) ፕሬዘደንት እና Clery PE Dariel (Later Danier Mar Philerinos) ዋና ጸሐፊ በማድረግ ሾሟቸዋል፡፡

**8. የኦርቶዶክስ ሲሪያን የሰንበት ትምህርት ቤት ኅብረት**

ይህ መንፈሳዊ ማኅበር የማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ ባለበት ዓለም በሙሉ ያለ አደረጃጀት ነው፡፡ የዚህ ሰንበት ትምህርት ቤት ማኅበር ዋና ዓላማ ለሕፃናት ትኩረትና እንክብካቤ በመስጠት መንፈሳዊ እውቀታቸውን በማሳደግ የጌታችን የኢየሱስ እና የመሠረታት ቤተ ክርስቲያን ተከታይ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

ሰንበት ትምህርት ቤቱ በከሬላ ግዛት ላሉት ሕፃናት በማለያለም (Malayalam) ቋንቋ ትምህርት የሚሰጥ ሲሆን፣ ከከሬላ ግዛት ውጪ ላሉት በዋናነት በእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ይሰጣል፡፡ በአደረጃጀቱም ክርስቲያኖች በብዛት ከሚገኙበት ከሬላ ውጪ ላሉት የተለየ ነው።

የሰንበት ትምህርት ቤቱ የትምህርት ክፍል ከቅድመ መደበኛ (Pre-primary) ክፍል እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል በተለያየ እርከን የተከፋፈለ ነው፡፡ እንደ አስኳላው ትምህርት (Secular schools) እስከ ዐሥረኛው ክፍል ያለውን የሁለተኛ ደረጃ የሰንበት ትምህርት ቤት ትምህርት ውጤታማ ሆነው ለጨረሱት የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ከፍተኛ የሁለተኛ ደረጃ ኮርስ በሚል ለሌላ ሁለት ተጨማሪ ዓመት እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ይማራሉ፡፡ የትምህርቱ ይዘት (Curriculum) በየጊዜው የሚሻሻል ቢሆንም፣ የሚከተሉት ከአኃት አብያተ ክርስቲያናት ጋር በጋራ የተዘጋጀውን እና የታተመው የትምህርት ሥርዓት ነው፡፡

የበጋውን የትምህርት ዕረፍት አስታኮ የሚሰጠው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት (The vacation Bible School) ለሁሉም ተማሪዎች ተደራሽ በመሆን እና የብዙዎችን ንቁ ተሳትፎም ያገኘ ነው፡፡ ማኅበሩ በየዓመቱ ለሰንበት ትምህርት ቤቶች የመማሪያ መጻሕፍት፣ የአምልኮ ቁሳቁሶችን (Devotional materials) ፣የመዝሙር መጻሕፍትን እና ካሴቶችን በማሳተም ለሁሉም ተደራሽ ያደርጋል፡፡

የማላንካራ ኦርቶዶክስ ሲሪያን ሰንበት ትምህርት ቤት ኅብረት የበላይ ጠባቂ ፓትርያሪኩ ሲሆኑ፣ ሦስት ሊቃነ ጳጳሳት የኅብረቱ ፕሬዝዳንት ናቸው።

ሊቀ ጳጳስ (H.G.Dr. Gabriel Mar Gregorios Metropolitan) በከሬላ ግዛት ላሉት ፕሬዝዳንት፤
ሊቀ ጳጳስ (H.G. Alexios Mar Eusebius) ከሕንድ ውጪ በሌሎች ዓለማት ላሉት ፕሬዝዳንት፤
ሊቀ ጳጳስ (H.G.Dr. Abraham Mar Seraphim) ከከሬላ ግዛት ውጪ ነገር ግን በሕንድ ሌሎች ግዛቶች ላሉት ፕሬዝዳንት ናቸው፡፡

እነዚህ እና የመሳሰሉት ሌሎች ዕድሜ ጠገብ በሆኑ አደረጃጀቶች ለቤተ ክርስቲያን የጀርባ አጥንት ሆነው አስፈሪ የሚመስሉ የመከራ ዘመናትን ተቋቋማ እንድታልፍና ዛሬ ላይ በመንፈሳዊ፣ ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ሀገራዊ እንቅስቃሴ ዙርያ ለምታደርገው አስደማሚ ሥራ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ያሏት መንፈሳዊ እና የልማት ተቋማት
የህንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን መንበረ ፓትርያርክ ኦኃዛዊ መረጃ እንደሚያመለክተው ቤተ ክርስቲያን

- 2 የሥነ መለኮት ኮሌጆች፣ ኮታይም እና ናግፑር ከተማ ላይ
- 12 የሴቶች ገዳማት (Convents)
- 24 ገዳማት
- 22 ማተሚያ ቤቶች
- 48 ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆች ማሳደጊያ (orphanages)
- 30 ሆስፒታሎች
- 4 የኢንጂነሪንግ ዩኒቨርሲቲዎች
- 9 የነርሲንግ ኮሌጆች
- 2 የሕክምና ዩኒቨርሲቲዎች
- 52 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች
- 10 የተማሪ ማረፊያ (ዶርሚተሪዎች) ያሏት ሲሆን ከዚህ ባሻገር ቤተ ክርስቲያን በሀገረ ስብከቱ እና በየአጥቢያዎቹ ድጋፍ (auspices) የሚደረጉላቸው
    - ※ በየመንደሩ( በአጥቢያ) የሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች
    - ※ ከሱስ ማገገሚያና መከላከያ ማእከላት
    - ※ የዓቅመ ደካሞች ማረፊያ ቤቶች
    - ※ የአእምሮ ሕመምተኞች መኖሪያዎች፣መጠለያ እና የመሳሰሉት ማእከላት ይገኛሉ፡፡

**ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ምን ተጠቀመች?**

1. የማላንካራ ቤተ ክርስቲያን በአገልግሎቷ ልዩ ከሚያደርጓት አንዱ ከሕፃናት ጀምሮ እስከ አረጋውያን ተሳታፊ (አካታች) የሚያደርገው አገልግሎቷ ተጠቃሽ ነው፡፡ ምእመናን በጋራ ተሰብስበው በቤተ ክርስቲያን ከሚደረገው የምስጋናና የጸሎት ተሳትፎ በዘለለ እስከ ቤተሰብ እና መንደር በዘለቀው የአገልግሎት አደረጃጀት ሁሉም ልጆቿ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ባይተዋር እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል።

2. ሕፃናትን በሰንበት ትምህርት ቤት ከማስተማር ባሻገር በቅዳሴ እና በሌሎች ወላጆቻቸው በሚገኙበት መርሐ ግብር ላይ ትምህርት እንዲያስተምሩ እና ዝማሬ እንዲዘምሩ ያደርጓቸዋል፡፡ ሁሉም ምእመናን እንደየ ትምህርት ዝግጅታቸው፣ እንደ የመንፈሳዊ እውቀታቸው፣ እንደ የዕድሜያቸው በተለያዩ መንፈሳዊ ማኅበራት ውስጥ ገብተው እንዲያገለግሉ ይደረጋል፡፡ በዚህም መሠረት ያላቸው አነስተኛ የምእመናን ቁጥር ሳይገድባቸው በማኅበራዊ፣ በምጣኔ ሀብት ትስስር እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ግንባር ቀደም በመሆን ተሰሚ እንዲሆኑና በብዙ አሕዛብ መካከል ተከብረው እንዲኖሩ አስችሏቸዋል፡፡

3. አንጋፋው የወጣቶች ማኅበር (የማር ጎርጎርዮስ የክርስቲያን ወጣቶች ማኅበር) ከሪል ስቴት ግንባታ እስከ ትልልቅ የንግድ ተቋማትን፣ከማተሚያ ቤቶች አንሥቶ የተለያዩ የገቢ ማስገኛ መንገዶችን እየቀየሰ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በሕንድ እና ከሕንድ ውጪ እንዲፋጠን በገቢ ረገድ ከፍተኛውን ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡

እ.ኤ.አ. በ2016 ማላንካራውያን ያስገነቡት በእስያ ትልቁ የተባለውና በቅዱስ ጎርጎርዮስ ስም የተነገባው ዓለም አቀፍ የካንሰር ሕክምና ማእከል (St. Gregorios International Cancer Care Centre) የዛሬ ልጆቿ ያላቸውን ዘመን ተሻጋሪ ሐሳባቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በየትኛው ዓለም መንፈሳዊውንም ዓለማዊውንም ዕውቀት ከገበዩ በኋላ ከዚህ በታች በተጠቀሱት መንፈሳዊና እና የልማት ተቋማት በመግባት በቋሚነት ሲያገለግሉ የእግዚአብሔርን መምሰል በብዙ ማትረፊያ መሆኑ የሚያስተምሩ ሕያዋን ምስክሮች መሆናቸውን ይረዳል፡፡

እኛም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናን ያሉንን ጥቂት የልማት ተቋማት እያጠናከርን፣የሌሉንን እየገነባን ወደፊት ብዙ ሥራዎች እንደሚጠብቁን እእያሰብን፣ ዛሬ ላይ ሕንፃ ገንብተን ለሱቅና ለቡቲክ ያከራየናቸውን ራሳችን እያስተዳደርንና ወደ ኮሌጆች፣ ሆስፒታሎች እና ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቀይረናቸው በዘመኑ ፍልስፍና እየጠፉ ያለውን ትውልድ መታደግና ለሌሎችም የበጎ ሥራ ተምሳሌት ልንሆን ይገባል፡፡

4. በሙሉ ሰዓት ተረጋግተው የሚያገለግሉ ካህናት እንዲኖራት ማድረግ፣

5. ወጣቶች ተመርቀው ሥራ በቀላሉ የሚያገኙባቸው ተቋማትን ማደራጀት መቻሏ ምእመናን፥ በመንፈሳዊውም ሆነ በዓለማዊ ኑሯቸው የተስተካከለ ሕይወት እንዲኖራቸው ማስቻል፣

6. የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሁሉ በኑሮ ራሳቸውን የቻሉ በመሆናቸው ተቸግሮ የሚለምን ሰው በአጥቢያ ደረጃ አለመኖሩ፣

7. በዓለማዊ ትምህርት የተማሩ ልጆቿ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተሻለ ሞሆኑን በማመን በሙሉ ጊዜ ለማገልገል እስከ ፕሮፌሰርነት የተማሩትን ትምህርት ትተው በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቻ ለመሳተፍ መወሰናቸው፣

8. በብዛት የተማሩት ልጆቿ በተለያዩ የዓለም ክፍላት ቤተ ክርስቲያንን ከማስፋፋት ባሻገር ለሀገራቸው ሕንድ እድገት ከፍተኛ እና ግንባር ቀደም ሚና መጫወታቸው፣

**እኛስ ከእነርሱ ምን እንማራለን?**

ከላይ ካየናቸው ከሕንድ ቤተ ክርስቲያን የምንወስደው ተሞክሮ

1. በኢኮኖሚ ራስን መቻል ምን ያህል የቤተ ሰብን መንፈሳዊ ሕይወት ብሎም የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት እንደሚያጠናክር፣

2. በዩኒቨርሲቲ ያለፉ እና ዘመናዊውን እውቀት ከጥልቅ ሃይማኖታዊ እውቀት ጋር አገናዝበው የያዙ ምሁራን እንደሚያስፈልጓት፣

3. የዘመናዊውን ዓለም ፈተና የተረዱ እና መሥዋዕትነት ለመክፈል የተዘጋጁ ካህናት ከአዲሱ ትውልድ መካከል መውጣት እንዳለባቸው፣

4. በተለይ ደግሞ  የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች እና የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች፣ የንስሓ አባቶች በመሆን የሚያገለግሉት ካህናት መንፈሳዊውን እውቀት ከዓለማዊው አጣምረው የያዙ መሆን እንዳለባቸው፣

5. አሁን ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የሚስተዋለው ችግር በከፊል “ሃይማኖት ጠል” የነበረው የኮሚኒስትና ሶሻሊስት አስተሳሰብ በሃገራችን ላይ የፈጠረው መሆኑን ተገንዝበን የተማረው እና አዲሱ ትውልድ ቤተ ቤተ ክርስቲያንን በክህነት በማገልገል እንደ የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ለውጥ ማምጣት እንደሚጠበቅብን፣

6. ከሁሉም በላይ የነገ ተረካቢ በሆኑት የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች እና የግቢ ጉባኤያት ላይ በትኩረት መሥራት እንዳለብን፣

7. በቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት እና የልማት እንቅስቃሴ ላይ በሙሉ ኃላፊነት እና ባለቤትነት መንቀሳቀስ እንዳለብን፣

8. ወጣቶች በተማሩት የአስኳላ ትምህርት ሙሉ ጊዜያቸውን በመስጠት እና የትርፍ ጊዜያቸውንም በመጠቀም የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በቴክኖሎጂ ውጤት እንዲደገፉ ማድረግ እንደሚቻል የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተሞክሮ ትልቅ ትምህርት ይሰጠናል።

# 5. ማኅበረ ቅዱሳን በማዕከላት

## የመቱ ማእከል አጭር ታሪክ

### ይዘት

- የኢሉባቦር ሀገረ ስብከት ዳራ
- በማኅበረ ቅዱሳን የመቱ ማእከል አመሠራረት
- ባለፉት ጊዜያት በመቱ ማእከል የተከናወኑ ዋና ዋና አገልግሎቶች
- በማእከሉ ያሉ ተግዳሮቶችና እገዛ የሚፈልጉ ሥራዎች

**1. የኢሉባቦር ሀገረ ስብከት ዳራ**

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥር ካሉት አህጉረ ስብከት የኢሉባቦር ሀገረ ስብከት በሀገሪቷ ቀደምት ከተመሠረቱ 4 አህጉረ ስብከት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህም ከንጉሥ ሐርቤ(ገብረ ማርያም) ከ1117-1157 ዓ.ም ጀምሮ ሲነሣ የነበረው የኢትዮጵያውያን ነገሥታትና ሊቃውንት ጥያቄ መልስ ሳያገኝ ቢቆይም ከበርካታ ዓመታት ትግል በኋላ የመጀመሪያዎቹ 4 ኢትዮጵያውያን ሊቃነ ጳጳሳት ግንቦት 21 ቀን 1921 ዓ.ም ግብፅ ካይሮ ጵጵስና ወስደው ከመጡ በኋላ በንጉሡ ትእዛዝ ከተከፈቱት አራት አህጉረ ስብከት ውስጥ የኢሉባቦር ሀገረ ስብከት አንዱ ነበር፡፡ ይህም በወቅቱ አጠራር «የምዕራብ ኢትዮጵያ ሀገረ ስብከት» እንደ ማለት ነው፡፡ በወቅቱ መንበረ ጵጵስናው የተመሠረተው በጥንታዊቷ ጎሬ ከተማ ነበር፡፡ የጎሬ ደብረ ገነት ቅድስት ማርያም ገዳምም የተመሠረተችው በ1875 ዓ.ም ነበር፡፡ ይህም የዐፄ ምኒልክ ሠራዊት ጦር መሪ ራስ ተሰማ ናደው ከሸዋ አራት ታቦታትን ከካህናት ጋር ይዘው መምጣታቸውን ተከትሎ የተመሠረተ እንደሆነ ይነገራል፡፡ በመቀጠል ከታቦቷ ጋር የመጡ ሌሎች ታቦታት ማለትም በቡሬ ወረዳ የሚገኝ የሰጠ ቅዱስ ሚካኤል፣ አደሌሰገ ሩፋኤልና ሱጴ ቅድስት ሥላሴ በዚሁ ዓመተ ምሕረት እንደ ተመሠረቱ ታሪክ ይናገራል፡፡

ምንም እንኳን ዕድሜ ጠገብ ሀገረ ስብከት ቢሆንም፣ ከመሐል ሀገር ባለው ርቀት እና በተለያየ ሁኔታ ካለው ፈተና ጋር ተዳምሮ ሀገረ ስብከቱ በሚገባው የአገልግሎት ደረጃ ላይ ነው ማለት አይቻልም። በአዲሱ ሀገረ ስብከት ቡኖ በደሌን ጨምሮ በሀገረ ስብከቱ ከ 380 በላይ አብያተ ክርስቲያናት ያሉ ሲሆን ከእነዚህ ዉስጥ ከ60 አብያተ ክርስቲያናት  በላይ ተዘግተዋል፡፡ አብዛኛዎቹ በዓመት የበዓላትን ቀን ምክንያት በማድረግ የሚከፈቱ ሲሆን ጥቂቶቹ ማለትም 7 አብያተ ክርስቲያናት ብቻ የሚገኙበት በኖኖሰሌ ወረዳ ያለው እንደ ዋካ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ዓይነቶቹ ደግሞ በዓመትም አንድ ጊዜ እንኳ የመከፈት ዕድል የላቸውም፡፡

በእነዚህ የተዘጉ ቦታዎች ክርስትና በ40 እና በ80 ማስነሣት አይታሰብም፤ ሰው ሲሞት ፍትሐት የለም፤ ምእመኑ መካሪና አስተማሪ ባለማግኘቱ ወደ ሌላ ሃይማኖት እየፈለሰ ይገኛል፤ ሲታመም የሚያጠምቀው ካህን ባለመኖሩ፣ «እንጸልይልህ» በሚለው የመናፍቃን ወከባ ሥር ይወድቅና በቀላሉ ሃይማኖቱን እየካደ ይገኛል፡፡ በእነዚህ ቦታዎች የኦርቶዶክሳውያን ቁጥር በእጅጉ እየቀነሰ ይገኛል፤ ይህ ደግሞ ለሌሎች ምቹ አጋጣሚን ፈጥሮላቸዋል፡፡ ኦርቶዶክሳውያን ከማኅበራዊ አገልግሎት እየተገለሉ ይገኛሉ፤ በሀገረ ስብከቱ ከ15 ቀበሌዎች በላይ ሙሉ በሙሉ የክርስቲያኖች ቁጥር ተመናምኖ በአሕዛብ በመሸፈኑ ክርስትና እንዳይስፋፋ አዲስ ቤተ ክርስቲያን የሚሠራበትን ቦታ "ሆ" ብለው በመውጣት አፍርሰዋል፡፡ ለምሳሌ፡-

- ※ ዳሪሙ ወረዳ ጉሪ ዑራኤል የእመቤታችን ሥዕል በአህያ ላይ አስረዋል፤
- ※ ጎርዶሞ ከተማ መስቀል በውሻ ላይ አስረዋል፤
- ※ ምጎርዶሞ ከተማ ሲቦ ከተማ ወዘተ ቦታዎች ላይ የቤተ ክርስቲያን መሬት ሙሉ በሙሉና በከፊል ተከፋፍለውታል፤
- ※ ያዮ ወረዳ ከሚሴ ቀበሌ ቁራ መድኃኔዓለም ከ11 ሄክታር በላይ መሬት ተከፋፍለዉ ቡና ተክለውበታል፤
- ※ በዲዱ የእሑድ ገበያ እንዳይቀየር ከፍተኛ ጫና የፈጠሩ ሲሆን በርካታ አፈናዎች፣ ማወከቦች እና እስሮች ክርስቲያኖች ላይ ደርሰዋል፤
- ※ በዲዱ ወረዳ ላሎ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን መቃብር ቤት ሳይቀር ወስደዋል፤ መቃብር ቤቱን ሱቅ አድርገዋል፡፡

እነርሱ መሐል ጥቂት ክርስቲያኖች ብቻ የሚኖሩ ከሆነ ከእድር ለማውጣት ማስፈራራት እና በማኅበራዊ ኑሮ ክርስቲያኑን ማግለል እየተሠራበት ይገኛል፡፡ ለምሳሌ፡-

※ ኖኖ ወረዳ፣ ላሎ ወረዳ፣ አሌ ወረዳ ...ወዘተ ብትሞቱ አንቀብራችሁም በማለት በማስፈራራትና በግድ እንዲሰልሙ ማድረግ፣

በከተሞች ያሉትን ነባርና ጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎችን መሬታችሁ በዝቷል በሚል ሰበብ ካርታ መከልከል፣ ለምሳሌ፡-

※ ቡሬ ጊዮርጊስ፣ ጎርዶሞ ኪዳነ ምሕረት፣ ብርብርሳ ሚካኤል፣ የጥምቀት ቦታዎችን መውሰድ፣ ነባር ቦታዎችን በስመ ልማት መንጠቅ፣

※ የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ሕጋዊ ፍትሕን መንፈግ፣

※ የቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ ነባር ይዞታዎችን ለመኖሪያ ቤቶች መሥሪያ ማከፋፈል፣ ለምሳሌ፡- ቡሬ፣ ዑካ፣ መቱ ማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ቤተ ክርስቲያን፣ የተሠራውን ቤተ ክርስቲያን አፍርሱ እስከ ማለት ደብዳቤዎችን መጻፍ፣ ለምሳሌ መቱ ቆሎ ኮርማ ጽዮን ቤተ ክርስቲያን፣ ዴጋ ቅድስት አርሴማ፣ ዑካዑምቤ ልደታ ቤተ ክርስቲያንን ወዘተ ቦታዎች ላይ የቤተ ክህነት ሰዎችን እስከ ማሰርና ምእመናንን እስከማዋከ ተደርሷል፡፡ ኦርቶዶክሱን ከወሳኝ የሥልጣን ቦታዎች የማሸሽ ተግባር ከቀበሌ እስከ ወረዳ እየተሠራበት ይገኛል።

ይህም ሆኖ ሀገረ ስብከቱ የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናት እንዲከፈቱ፣ የቤተ ክርስቲያን መብት እንዲከበር፣ የአብነት ትምህርት ቤት እንዲስፋፋ ለማድረግ፣ ከማእከሉና ከማኅበራት ኅብረት ጋር ለመሥራት እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ እንደ መልካም እርምጃ የሚታይ ነው።

**2. በማኅበረ ቅዱሳን የመቱ ማእከል አመሠራረት**

መቱ ማእከል በምዕራብ ኢትዮጵያ የኢሉባቦር ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና ካለበት መቱ ከተማ፣ ከአዲስ አበባ ደግሞ 600 ኪሎ ሜትር ርቆ ይገኛል። መቱ ማእከል በማእከል ደረጃ የተመሠረተው በ 1992 ዓ/ም ነው። የመቱ ማእከል ወደ ማእከልነት ከማደጉ በፊት በጅማ ማእከል ሥር እንደ አንድ ወረዳ ማእከል ሆኖ ሲያገለግል የነበረ እና በኢሉባቦር ሀገረ ስብከት ደረጃ በንዑስ ማእከልነት መቋቋም አለበት ተብሎ በንዑስ ማእከልነት ለበርካታ ዓመታት አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቶ በ1992 ዓ.ም ወደ ማእከልነት ማደግ ችሏል፡፡ በሰኔ 2015 ዓ/ም የበደሌ ወረዳ ማእከል አዲስ የተዋቀረ ሀገረ ስብከትን ተከትሎ በሥሩ ያሉትን መዋቅሮች በማካለል ወደ ማእከልነት እስካደገ ጊዜ ድረስ፣ የመቱ ማእከል ጽ/ቤቱን የሀገረ ስብከቱ መቀመጫ በሆነችው መቱ በማድረግ 16 ወረዳ ማእከላትን፣ 5 ግንኙነት ጣብያዎችን፣ 4 የግቢ ጉባኤያትን፣ ከ350 በላይ አባላትን በመያዝ ሲያገለግል ቆይቷል። በአሁኑ ወቅት መቱ ማእከል 10 ወረዳ ማእከልና 3 ግንኙነት ጣብያዎች፣ 3 ግቢ ጉባኤያት፣ ከ300 በላይ አባላት ያሉት ማእከል ነው።

ማኅበረ ቅዱሳን መቱ ማእከል ከመመሥረቱ ቀድሞ መነሻውን ጅማ ያደረገ የሦስት ቀን ጉባኤና በዋና ዋና ከተሞች የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በወንድሞችና እኅቶች ይዘጋጅ ነበር። ማእከሉ ከተመሠረተ በኋላ በወረዳዎች ላይ የስብከተ ወንጌል ጉባኤ ማዘጋጀት፣ በጤና ተቋም እና በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት ላይ ግቢ ጉባኤያትን ማቋቋም እና ማስተማር፣ ሐመር መጽሔት፣ ስምዓ ጽድቅ ጋዜጣ እና መለከት መጽሔቶችን ማሠራጨት፣ በገጠር አብያተ ክርስቲያናት ላይ የሰንበት ት/ቤቶችን ማቋቋም እና ማስተማር የመሳሰሉትን ማከናወን ጀመረ፡፡ ማእከሉ ከተመሠረተበት ጊዜ አንሥቶ በየደረጃው ካሉ የቤተ ክህነት መዋቅር ጋር በቅርበትና በተግባቦት በመሥራት ይታወቃል።

ማእከሉ ከተመሠረተበት ጊዜ አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ ያከናወናቸውን ዋና ዋና ተግባራት ለመጥቀስ፥ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ወንጌል እንዲማሩ ማድረግ፣ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ሰንበት ት/ቤቶችን መመሥረት፣ አብያተ ክርስቲያናት ባልተመሠረቱበት ላይ እንዲመሠረቱ ማድረግ፣ ንዋያተ ቅድሳት ባልተሟላላቸው አብያተ ክርስቲያናት እንዲሟላላቸው ማድረግ፣ የተላያዩ ፕሮጀክቶችን በማጥናት ተግባራዊ ማድረግ፣ የአብነት ት/ቤቶችን ማቋቋም እና መደገፍ፣ በተለያዩ ርእሶች ላይ ለካህናት፣ ለሰንበት ት/ቤቶች  እና ለምእመናን ሥልጠና መስጠት፣ ለተተኪ መምህራን ሥልጠና ማዘጋጀት እና መስጠት፣ በ2020 ፕሮጀክት ለካህናት እና ከሰ/ት/ቤቶች ለተወጣጡ ሥልጠና መስጠት፣ ሐዊረ ሕይወት በማዘጋጀት ምእመናን በሃይማኖት እንዲበረቱ ማድረግ፣ 1980 ዎቹ  ዓ.ም በበደሌ ወረዳ የተሐድሶ መናፍቃን በማጋለጥ እንዲለዩ ማድረግ፣ እንዲሁም 2010 ዓ/ም በመቱ ተመሳሳይ ሥራ ተሠርቷል፡፡ ግቢ ጉባኤያትን ማቋቋም እና ማስተማር፣ ቅድመ ግቢ ጉባኤ ማቋቋም እና ማስተማር እንዲሁም ሥልጠናዎችን መስጠት ይጠቀሳሉ።

በእነዚህ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በብዙ መልኩ በጎ ተጽእኖ ማሳደር ችሏል። ከእነዚህ ውስጥ ከቤተ ክርስቲያን የራቁ ምእመናን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲቀርቡ፣ ሃይማኖታቸውን እንዲያውቁ፣ የተሐድሶ መናፍቃንን ሴራ እንዲረዱ በማድረግ ለቤተ ክርስቲያን ዘብ እንዲቆሙ አድርጓል፡፡





# ፫. ባለፉት ጊዜያት በመቱ ማእከል የተከናወኑ ዋና ዋና አገልግሎቶች

በዋና ማእከል አስተባባሪነት በሰሌ ኖኖ ወረዳ ቤተ ክህነት የሳርዶ ማርያም የብፁዕ አቡነ ሚካኤል (ዶ/ር) መታሰቢያ አብነት ትምህርት ቤት ከ 4 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ ተገንብቷል። በሀገረ ስብከቱ ከሚገኙት ከ380 በላይ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ 179ኙ ብቻ በቂ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጥባቸው ሲሆኑ፣ 141ዱ አንድ ቄስ እና ዲያቆናት ብቻ ያሏቸው በመሆናቸው ቅዳሴ የማይካሄድባቸው እና 60ው ደግሞ ጭራሹኑ ተዘግተው የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡ ሀገረ ስብከቱም ሰፊ ሲሆን፣ በተለይ ከመቱ ከተማ በስተቀር ሌሎቹ በገጠር በሚገኙ ትንንሽ ከተሞች ያሉት አገልጋዮች ጥቂት ከመሆናቸውም በተጨማሪ ከሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የሚመጡ ስለሆነ የአካባቢውን ቋንቋ(ኦሮምኛ) ተናጋሪ ባለመሆናቸው ወንጌል አስተምሮ እና ሰብኮ ምእመኑን በሃይማኖቱ እንዲጸና ማድረግ ላይ ባሉ ውስንነቶች መግባባት ስለሚያቅታቸው ብዙም ሳይቆዩ ገሚሶቹ ጥለው ይሄዳሉ፡፡ የቀሩትም ቢሆን ከሥርዓተ ቅዳሴ ውጪ ሌሎች መንፈሳዊ አገልግሎቶችን ለምእመኑ መስጠት አይችሉም፡፡ በዚህም ምክንያት ምእመናን በቂ መንፈሳዊ አገልግሎት ስለማያገኙ፣ ሃይማኖታቸውን ባለማወቃቸው እና ኑሯቸውም ዝቅተኛ በመሆኑ በየጊዜው በትንሽ ጥቅማ ጥቅም እየተደለሉ ከእነልጆቻቸው ወደ ሌላ እምነት እየሄዱ ይገኛሉ፡፡ ይህ ችግር በዚህ ከቀጠለ ወደ ፊት የሚፈጠረውን ችግር በማሰብ የተሠራው ይህ አብነት ትምህርት ቤት ወደ ሥራ የገባ ቢሆንም በሙሉ ዓቅሙ ፍሬ እንዲያፈራ የመምህራን፣ የቁስ እና የበጀት ድጋፍ ይፈልጋል።



አብነት ት/ት ቤቱ በተሠራበት ቦታ ቀድሞ የነበረ ቤተ ክርስቲያን



የአብነት ት/ት ቤቱ ምረቃ

# ሐዋርያዊ ተልእኮ



## 3.1. በሐዋርያዊ ተልእኮ ጉዞዎች የመጡ ለውጦች

ባለፉት 10 ዓመታት መቱ ማእከል እና በሥሩ ያሉት ወረዳ ማእከላት በርከት ያሉ ሐዋርያዊ ጉዞዎችን አድርገዋል፡፡በእነዚህም ሐዋርያዊ ጉዞዎች ለአጥቢያዎች የወንጌል አገልግሎትን ከማዳረስ በተጨማሪ ለቤተ ክርስቲያን መሥሪያ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ዕርዳታ ለማድረግ ችለዋል፤ ሕዝበ ክርስቲያኑ በሃይማኖቱ እንዲጠነክር ተደርጓል፤ በአንዳንድ ስፍራዎች በአንድ ሐዋርያዊ ጉዞ የተገነቡ አብያተ ክርስቲያናት ጭምር አሉ። ለምሳሌ፡- የኡካ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ይጠቀሳል፡፡

## 3.2. ሐዊረ ሕይወት

መቱ ማእከል ምእመናንና አገልጋዮችን በማስተባበር በተለያዩ ጊዜያት ሐዊረ ሕይወት መርሐ ግብር አካሂዷል። ሐዊረ ሕይወት ወይም የሕይወት ጉዞ ሊ.ቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን፣ ምእመናንን፣ የሚሄድበትን ደብርና የአካባቢውን ሕዝበ ክርስቲያን በማቀፍ ወደ ታሰበ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ የሚከናወን የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ነዉ፡፡ በመርሐ ግብሩ ከ2-3 ክፍል የስብከተ ወንጌል አገልግሎት፣ ምክረ አበው፣ መጣጥፎች፣ ያሬዳዊ ዝማሬ እና ለቤተ ክርስቲያኑ መባ የማሰባሰብ መርሐ ግብር የሚከናወኑበት ነበር፡፡ በመቱ ማእከል ከጥር 25 ፤ 2016 ዓ/ም ጀምሮ ወደ ተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የሐዊረ ሕይወት ጉዞዎች ተካሂደዋል። ለምሳሌ በመቱ ወረዳ ቤተ ክህነት አገሎ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን፣ በኡካ ወረዳ ቤተ ክህነት የቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን፣ በመቱ ወረዳ ቤተ ክህነት በሴጎ ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን እና በሁሩሙ ወረዳ ቤተ ክህነት በኮንቼ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያንን ከቀዳሚዎቹ መጥቀስ ይቻላል። ሐዊረ ሕይወት ክርስቲያናዊ ኅብረትን ከማጠናከር ጭምር ስብከተ ወንጌልንና ሐዋርያዊ ተልእኮን ለመፈጸም የጠቀመ ነው።



## 3.3. የስብከተ ወንጌል ማስፋፊያ ፕሮጀክት እንቅስቃሴ

ይህ የስብከተ ወንጌል ማስፋፊያ ፕሮጀክት በኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን ዋና ማእከል በተመረጡ 20 አህጉረ ስብከት ውስጥ፣ በተመረጡ 100 ወረዳ ቤተ ክህነት ላይ ለመተግበር ለ10 ዓመት የተያዘ ፕሮጀክት ነው፡፡ ከ20 አህጉራተ ስብከት ውስጥ የኢሉባቦር ሀገረ ስብከት ያለበት ሲሆን መቱ፣ ጎሬ፣ ደምቢ፣ ያንፉና ዶረኒ አምስቱ የተካተቱ ወረዳ ቤተ ክህነቶች ናቸው፡፡ የዚህ ፕሮጀክት ዋና ዓላማ በተለያዩ ምክንያቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ያለውን የምእመናንን ቁጥር ለመታደግ፣ ያላመኑትን ለማሳመንና ለጥምቀተ ክርስትና ለማብቃት፣ ያመኑትን በማጽናት በርትዕት ሃይማኖት ለማቆየት እና አምነው ያሉትን ከምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን እንዲሳተፉ ለማድረግ የታሰበ ነው፡፡

በዚህ ፕሮጀክት የተከናወኑ ተግባራት በተለያዩ በተመረጡ አብያተ ክርስቲያናት ሞዴል ጉባኤዎችን በማካሄድ ወንጌለ ክርስቶስን መስበክ፣ በክረምት ሥልጠና ከሰ/ት/ቤት ለተወጣጡ አባላት አጫጭር ሥልጠናዎችን መስጠት፣ ለካህናት አባቶች ሥልጠና መስጠት፣ ለአንዳንድ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፣ ለመምህራነ ወንጌል ድጎማ ማድረግ ወዘተ ናቸው። ዶረኒወረቦ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን፣ በዶረኒ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ላይ የተካሄዱ ጉባኤዎች፣ በጎሬጉመሮ አቦ ቤተ ክርስቲያን (በዚህ ፕሮጀክት ጥሩ እንቅስቃሴ የተደረገበት ወረዳ ማእከል እና ውጤትም የመጣበት ነው።)፣ ደምቢ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን፣ መቱ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል እና በማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ላይ የተካሄዱትን ማንሣት ይቻላል፡፡

## 3.4. የተተኪ መምህራን ሥልጠና

- አዲስ አበባ መጥተው ክረምት ክረምት፥ የተተኪ ሥልጠና የወሰዱ የሠልጣኞች ብዛት 13
- ሠልጥነው ያሠለጠኗቸው የሠልጣኞች ብዛት 500
- አሁን በድጎማ በማኅበሩ እያገለገሉ ያሉ መምህራን ብዛት 7
- በአብነት ት/ት እየተማሩ የሚገኙ ተማሪዎች 221



## 4. በማእከሉ ያሉ ተግዳሮቶችና እገዛ የሚፈልጉ ሥራዎች

### 4.1 ተግዳሮቶች

በሀገረ ስብከቱም ሆነ በማእከሉ ብዙ ተግዳሮቶች ቢኖሩም፥ ማእከሉ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በወቅታዊ ፈተና ሳይሸነፍ ብዙ ፈታኝ ጊዜያትን አልፏል። ከላይ በዝርዝር እንዳየነው በሀገረ ስብከቱ ያሉ ምእመናን በብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ ይገኛሉ። ማእከሉ በሚገኝበት ሀገረ ስብከት ከ 60 በላይ አብያተ ክርስቲያናት መዘጋት፣ ከኦርቶዶክሳውያን የጸዳ ቀበሌ የመመሥረት ሴራ፣ በክርስቲያኖች ላይ እየተፈጸሙ ያሉ ጫናዎች፣ ፖለቲካ ለበስ ወቅታዊ ጫናዎች ፣ መንግሥታዊ መዋቅርን ተጥቅሞ የሚፈጠሩት ጫናዎች፣ የክርስቲያኖችን ኢኮኖሚ ለማዳከም እየተሠሩ ያሉ ደባዎች እና በተለያዩ ምክንያቶች የምእመናን ቁጥር መቀነስ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ማእከሉ ምሳሌ መሆን በሚችል መልኩ ውጭ ካሉ የአከባቢው ተወላጆች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለአገልግሎት የሚረዱ ሦስት ሞተር ሳይክሎችን በማስግዛት እየተጠቀመ ቢገኝም ሌሎችእገዛ የሚፈልጉ ሥራዎች አሉት።

### 4.2 እገዛ የሚሹ ሥራዎች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ማእከሉ የበለጠ እንዲሠራ እገዛን የሚፈልጉ ናችው።

- ማእከሉ የራሱ የሆነ ጽ/ቤት የሌለው በመሆኑ የጽ/ቤት ግንባታ፣
- ለሳርዶ አብነት ት/ት ቤት ተጨማሪ ድጋፍ፣
- የማእከሉን የማስፈጸም ዓቅም ማሳዳግ፣
- የቁሳቁስ ድጋፍ፣
- ያሉትን ሌሎች አብነት ት/ቤት ማጠናከር፣
- የካህናት ሥልጠና በትምህርተ ኖሎት እና በክብረ ክህነት ዙሪያ በሁሉም ወረዳዎች መስጠት፣
- የተተኪ ሰባክያነ ወንጌልን ሥልጠናን በሁሉም ወረዳዎች መስጠት፣
- የስብከተ ወንጌል ኬላዎችን ማቋቋም እና አገልግሎትን ማጠናከር፣
- በሁሉም ወረዳዎች አገልግሎትን የሚያስተባብር መደበኛ አስተባባሪ እንዲኖር ማድረግ፣
- በሙቱ ከተማ የግእዝ ቋንቋ ፕሮጀክት መተግበር... ወዘተ በዕቅድ የተያዙና የምእመናንን ድጋፍ የሚሹ ሥራዎች ናቸው።።



# 6. ቤተ አናግድ

**ቃለ መጠይቅ ከመልአከ ሰላም ታዬ አብርሃም ጋር**

ሰላም ውድ አንባብያን! የዛሬ እንግዳችን መልአከ ሰላም መምህር ታዬ አብርሃም ይባላሉ። መልአከ ሰላም መምህር ታዬ አብርሃም(ጋሽ ታዬ) በእግዚአብሔር ጥሪ ቃለ እግዚአብሔርን ለማስተማር የተጠሩ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል ከስልሳ ዓመታት በላይ ያስቆጠሩ፣ በመላዋ ኢትዮጵያ እየዞሩ ሲያስተምሩ እና ስለ ተዋሕዶ ሃይማኖት ሲመሰክሩ የኖሩ፣ ከ፲፱፻፶ወ፱ ዓ.ም. ጀምሮ በምስካዬ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም የተምሮ ማስተማር ማኅበር (ሰ/ት/ቤት) አባል የሆኑ እና በቡራዩ የሚገኘው የጽርሐ ጽዮን አንድነት ኑሮ ማኅበር መሥራቾች መካከል አንዱ ናቸው።

በተጨማሪም በዳግማዊት ኢየሩሳሌም ደብረ አሚን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም የምክሐ ደናግል የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር፣ በተለያዩ ሰንበት ትምህርት ቤቶች እንዲሁም በማኅበረ ቅዱሳን እና በልዩ ልዩ  መንፈሳዊ ማኅበራት ሰፊ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ሲሰጡ የኖሩ እና አሁንም ከልዩ ልዩ እምነት ለሚመጡ ሰዎችም ጭምር የምክር አገልግሎት በመስጠት ዘርፈ ብዙ የሕይወት ውጣ ውረድ የሚገጥማቸውን ሰዎች በመምከር ብዙዎችን እየጠቀሙ የሚገኙ አባት ሲሆኑ ከእንግዳችን ጋር ያደረግነውን ቃለ መጠይቅ ቀጥሎ እናቀርብላችኋለን፤ ትከታተሉን ዘንድ በአክብሮት እንጋብዛለን!

**መጽሔት ተልእኮ**፡- መልአከ ሰላም ጥያቄያችንን ተቀብለውና ጊዜዎትን ሰጥተው ጥያቄዎቻችንን ለመመለስ ፈቃደኛ ስለሆኑልን በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን። ሰንበት ትምህርት ቤት ማለት ምን ማለት ነዉ፤ ይህን ስምስ እንዴት አገኘ?

**መልአከ ሰላም**:- እሺ እግዚአብሔር ይስጠልኝ! ከጥንት በቤተ ክርስቲያናችን ሰ/ት/ት ቤት የሚባል አልነበረም፤ የመጣው በኋላ ነው፡፡ እያንዳንዱ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚቋቋሙ ማኅበራት የሚጠሩት በወጣት ማኅበር እንጂ በሰ/ት/ት ቤት ስም አልነበረም፤ ተምሮ ማስተማር በማኅበር ስም ነበር የሚጠራው፤ በእርግጥ ማኅበር የሚለው ስምም ቤተ ክርስቲያናዊ ነው፤ ሰንበቴም ጽዋዓም እንዲሁ በነቢያቱ፣ በሐዋርያቱ፣ በቅዱሳኑ፣ በጻድቃኑ እና በሰማዕታቱ ስም እየሰየሙ ይሰበሰቡ ነበር፡፡ ታዲያ በኢትዮጵያ እግዚአብሔር የለም የሚል ፍልስፍና ይራመድ ስለነበር ትውልዱ ከእግዚብሔር እንዲርቅ የሚፈልሚጉ አካላት ስለነበሩ ማኅበር እየተባለ የሚጠራ ሁሉ እንዳይኖር ተጽእኖ ስላደረጉ ሲኖዶሱ ግድ ሆነበት፤ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር የሚለው ስም ተለውጦ “Sunday School” የሚል የውጪዎቹ የውሰት ስም ተሰጥቶት እና በቃለ ዓዋዲው እንዲገባ ተደርጎ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ እንደ ሁልጊዜው ቤተ ክርስቲያን የውስጥም የውጭም ጠላቶች (ፈተናዎች) ነበሩባትና እንዲህ ስሙ ሊቀየር ችሏል፡፡ ሰ/ት/ት ቤት ማለት ደግሞ ቃለ ዓዋዲ እንዳሰፈረው በሰንበት ቤተ ክርስቲያን እየተሰበሰቡ የሚማሩ ሕፃናትና ወጣቶች ማለት ነው፡፡

**መጽሔተ ተልእኮ**:- የሰ/ት/ት ቤት ዓላማ ምንድው በእነማንና መቼ ተመሠረተ?

**መልአከ ሰላም**:-ዓላማው ለቤተ ክርስቲያን ተተኪ ምእመናንን፣ ቀሳውስትን እና ዲያቆናትን በጠቅላላ አገልጋዮችን ማፍራትና ወጣቱ ትውልድ ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ሃይማኖቱን ጠብቆ ከመናፍቃን ቅሠጣ እንዲሁም ከዓለማዊነት እንዲድን ነው፡፡ አመሠራረቱ ደግሞ ሃይማኖት የግል ሀገር የጋራ ተብሎ በታወጀ ጊዜ በተለያየ ጊዜና ቦታ ቤተ ክርስቲያን በውጭ ወራሪ እንዳትወረር ልጆቿንም በዘመናዊ መንገድ የምታደራጅበት መንገድ ሳይመቻች ስለነበር በዚህ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በጣም አዝነው አንዳንድ እንቅስቃሴዎችንም ጀምረው ነበር፡፡ ለምሳሌ:- የተምሮ ማስተማር ማኅበር ሊመሠረት የቻለው በ1935 ዓ.ም ለሃይማኖታቸው በሚቆረቆሩ ወጣቶች ነው፡፡ ከእነዚህም መካከል በሕይወት የሌሉ ቀሲስ ታደሰ መንግሥቱ አቶ አበበ ከበደ ሲሆኑ በሕይወት ካሉት ደጅ አዝማች ወልደ ሰማዕት ገብረ ወልድ እና አባ መዓዛ ቅዱሳን ገብረ ሕይወት ይገኙበታል፡፡ እኔ ስማቸውን ያልጠቀስኳቸውም ብዙዎች ናቸው፡፡ ተጨማሪ እንይ ካልን ደግሞ እንደነ ግቢ ገብርኤል (ዓምደ ሃይማኖት) ያሉት መምህር ቀጸላ የሚባሉ ብፁዕ አቡነ እንድርያስ የጥንቱ ናቸው የመሠረቱት፡፡

**መጽሔተ ተልእኮ**:- ሰንበት ትምህርት ቤት እና ክርስቲያናዊ ሕይወት በምን ይገለጻል?

**መልአከ ሰላም**:- ቤተ ክርስቲያን ስንል ሁሉን ያቀፈች ናት፤ በግልገሎች የተመሰሉ ሕፃናት፣ በጠቦቶች የተመሰሉ ወጣቶችንና በእናት በግ የተመሰሉ ወላጆችን የምታጠቃልል ናት፡፡ ስለዚህ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን መገኘት፣ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት መማር፣ በወንጌል መመራት፣ ሕግጋቱን መጠበቅ፣ እግዚአብሔርን መፍራት፣ ፍቅረ ቢጽ እና ፍቅረ እግዚአብሔርን ማወቅ በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያንን ማወቅ እስከሚፈቀድለት ድረስ ማጥናት አለበት በዚህም ሕይወቱ ይገለጻል፡፡

**መጽሔተ ተልእኮ**:- የሰንበት ትምህርት ቤት አገልጋዮች እስከመቼነው ቆይታቸው? (ሰንበት ተማሪነታቸው) በተለያ ተግዳሮቶች የሚያቋርጡ አሉ፤ እስከ ሕይወታቸው ሕቅታ (ፍጻሜ) ደግሞ ባሉበት ጸንተው በነበሩበት አገልግሎት የሚቀጥሉም አሉ፤ አብዛኛው ደግሞ በልዩ ልዩ ሁኔታ በትዳር፣በሥራና በኑሮ ሁኔታ በሚያጋጥሙ ቀላልና ከባድ አሳማኝ በሆነ በማያሳምንም ምክንያት የመራቅ ነገር አለ፤ ከዚያ አንጻር እስከመቼ ነው ሰንበት ተማሪ ሆኖ መኖር ያለበት?

**መልአከ ሰላም፡- “እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል”** (ማቴ.24፥13) እንደተባለ ክርስቶስን መከተል ለጊዜው አይደለም። በሕፃንነት በወጣትነት የጀመሩትን እንዲቀጥሉበትና ቤተ ክርስቲያንን እንዲረከቡ ነው እንጂ አግብቻለሁ ስለዚህ አሁን አይመቸኝም እንዲሉ አይደለም፡፡ እኔ ከማውቀውና ከተምሮ ማስተማር የተማርኩት በልጅነታቸው ጀምረው አግብተው ልጅ ወልደው ከቤተ ክርስቲያን አይርቁም፡፡ በዓለማዊም በመንፈሳዊም ሕይወታቸው ብዙ ኃላፊነት አለባቸው፤ ነገር ግን ሁሌም አሉ፡፡ ምክንያቱም ለአገልግሎቱ ጥልቅ ፍቅር ስላላቸው ነው፡፡ እስከ ተወሰነ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ሰንበት ተማሪ መሆን ካገቡ በኋላ ደግሞ መጥፋት አይቻልም። ቤተ ክርቲያን የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ናት፡፡ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን እየቀረበ ይሔዳል እንጂ በሰበብ አስባቡ እና በዚህ ዓለም ድካም ክርስቶስን አላገለግልም አይልም፡፡ ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል እስከ ሞት ነው!

**መጽሔተ ተልእኮ**፡- በሰንበት ትምህርት ቤት ተምሮ ያለፈና ደግሞ ሳይማር እንዲሁ ያለ ሰው ምንድነው ልዩነቱ፣ ከአስተዳደራዊና ከሃይማኖታዊ ዕውቀት፣ ከመንፈሳዊና ከሥጋዊ ሕይወት አንጻር ምን ይመስላል?

**መልአከ ሰላም**፡- ልዩነት አለው፤ በሰንበት ትምህርት ቤት አባል ሆኖ መኖር በመንፈሳዊ ሆነ በዓለማዊ ሕይወት ትልቅ ዕውቀት ይኖረዋል። የተሰጠንን የተቀበረ መክሊታችንን ለቤተ ክርስቲያን እንድናወጣ ስንደረግ እግረ መንገዱን በዓለማዊ ሕይወት ለሚገጥሙን ፈተናዎች መውጫ መንገድ በመሆን ጠቅሞናል፡፡ ሰንበት ተማሪ በመናፍቃን አይደለልም፤ መንፈሳዊነትና ለሰዎች አርዓያነትም ይኖረዋል፤ ጥበብ ነክ ነገሮች እንዲያድጉ ያደረጉት እኮ ከሰንበት ትምህርት ቤት የወጡ ልጆች ናቸው። መምህር ቢሆኑ ተግተው ያስተምራሉ፤ በምግባር ያንጻሉ፤ ዳኛ ቢሆኑ ጉቦን ይጸየፋሉ፤ የአእምሮ ንቃትም አላቸው። ወደ እራሴ ሕይወት ብመጣ እንኳ እኔ ምንም የማላውቀው በግ ዘመናዊ ትምህርት ተምሬአለሁ፤ ከተማ ስመጣ ትምህርቴን ለመቀጠል ነበር፤ ተምሮ ማስተማር መማሬ ግን ለሥጋዬም ለነፍሴም ጠቅሞኛል፤ አሁንም አለሁ ዕድሜዬ ትልቅ ቢሆንም ሰንበት ተማሪ ነኝ ። ከሁሉ በላይ ከሕጻናት ጀምሮ እስከ ዐዋቂ አንድ ቤተ ሰብ ያደርጋል። ሰንበት ትምህርት ቤት የተመሠረተ ፍቅር አይጠፋም። ብዙዎቹ ደግሞ በሥርዓተ ተክሊልና ቁርባን እንዲያገቡ ረድቷቸዋል፤ ለምንኩስና፣ ለምነናና ለጵጵስና ያበቃቻቸውም አሉ። በተጨማሪም አብረን እንኑር ብለው፣ የራሳቸውን መንደር ሠርተውና ጽርሐ ጽዮን ብለው ሰይመው ለመንደሩ አርአያ ሆነው ወንጌልን በተለያየ ቋንቋ እያስተማሩ የሚገኙም አሉ፡፡ ማኅበረ ቅዱሳንም የሰንበት ትምህርት ቤት ፍሬዎች ናቸው። በፊት እኮ ሰርግ በጭፈራ ነበር፤ ሰንበት ተማሪ ነው እሱን አስቁሞ በመዝሙር ያደረገው። በየትኛውም አገልግሎት ከሰንበት ትምህርት ቤት ያልወጣ የለም አብዛኛው ለቤተ ክርስቲያን የጀርባ አጥንት ሆኗል ቢባል እኔ አጋንኜ አልቆጥረውም። ቅኔ ተቀኝ፣ ማኅሌታይ፣ የዘመኑን ሊቃውንት ሁሉ ያገኘነው ከሰንበት ትምህርት ቤት ነው ስንቱ ተነግሮ ያልቃል ብዙ ነው ያደረገችልን!

**መጽሔተ ተልእኮ**፡- ከዚህ ጋር በተያያዘ ሰንበት ትምህርት ቤት ባልመጣ ምን እሆናለሁ ብለው ያስባሉ?

**መልአከ ሰላም**፡- ያው እንደ ኅብረተሰቡ ነበር የምሆነው፤ ወይ ደግሞ ጊዜ የማሳልፍበት ሳጣ ከአዛውንቶች ጋራ ካቲካላ ቤት ተገኝቼ ልሰክር እችላለሁ። ሰው ሥራ ሲፈታ ነው የሚሰክረው። ሎጥ እንኳ ከለመደው ቦታ ስለወጣ ነው እግዚአብሔርን አሳዝኖ የነበረው በንስሓ ተመለሰ እንጂ። ሥራ ፈት አእምሮ የሰይጣን ቢሮ ነው ። ሰንበት ትምህርት ቤት መዝሙር፣ ቅዳሴ፣ ወንጌል ማስተማር ነው ሥራዋ፤ በዚህ ውስጥ ስላለፍኩ ለነፍሴ ጠቅማኛለች።

**መጽሔተ ተልእኮ**፡- ጥያቄያችንን እያጠቃለልን ነው። የሰንበት ትምህርት ቤት መልካም አጋጣሚዎች እና ፈተናዎች ምንድን ናቸው?

**መልአከ ሰላም፡-** ሰንበት ትምህርት ቤት የቤተ ክርስቲያን አካል ስለሆነ ብቻውን አይፈተንም፤ ቤተ ክርስቲያን በተፈተነች ቁጥር በእርሷ ውስጥ ያሉ ሁሉ ይፈተናሉ፤ ፈተናውም በየዘመኑ ይለያያል። ፈተና በአንድ በኩል ጥሩ ነው፤ ወንጌል እንዲስፋፋ ያደርጋል። ይህን መልካም አጋጣሚ ልንለው እንችላለን። ሰንበት ተማሪዎች ከባድ የሕይወት ፈተና ሲመጣ ወደ ኋላ ሳያፈገፍጉ፣ ሥርዓት ባለው መንገድ ተጉዘው፣ ሰንበት ትምህርት ቤታቸውን ጠብቀው፣ ለቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ አድርገውና ጸንተው ለሌላ አርአያ የሆኑ አሉ።

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** በስተመጨረሻ ፈተና በበዛበት በዚህ ዘመን ላለ ወጣት ምን ዓይነት መልእክት ያስተላልፋሉ?

**መልአከ ሰላም ፡-** ለዚህ መጽሐፈ መክብብ ምዕራፍ 12 ጥሩ ምክር ይሰጣል። የችግር ዘመን ሊመጣ ይችላል። ሁል ጊዜ ደስታ የለም፤ ወጣቱ ከእግዚአብሔር ይልቅ ደስታን መውደድ የለበትም። ብዙዎቹ ክርስቶስን በመከተላቸው ሰማዕት የሆኑ ቅዱሳን አሉ፤ እነርሱን መመልከት፣ ገድላቸውን ማንበብ ጥሩ ነው፤ ሕይወታቸው አስተማሪ ነው። የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ስለሆነ ፈቃዱን ለመፈጸም የሚያስቀድም፣ የሚያቅደውም ያዕቆብ 4፥15 ላይ እንደተጻፈው ከእግዚአብሔር ጋር ይሁን፤ ከንስሓ አባቱም ጋር ይነጋገር፤ ምክር ይጠይቅ፤ ጊዜውን በዋዛና ፈዛዛ አያሳልፍ፤ ይልቁንም በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደትም መበርታትን ይልመድ። ከስካር፣ ከሱስና ከዝሙት መራቅ፣ ትዕግሥት፣ የዋኅነትና ትሕትና ያስፈልጋል፤ ሁሉን ይፈትሽ ይመርምር። በአጠቃላይ መንፈሳዊ ትጥቅ መታጠቅ አለበት።

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር!**

# 6. ይናገራል ፎቶው



ከሰሜን ሸዋ ሰላሌ ፍቼ ሀገረ ስብከት የተለያዩ ወረዳዎች ለተፈናቀሉ 40 ካህናት የተደረገ ድጋፍ።



ሰቆጣ ለሚገኙ ከወሊጋ ለተፈናቀሉ ወገኞች የተደረገ ድጋፍ



ከሰሜን ሸዋ ሰላሌ ፍቼ ሀገረ ስብከት የተለያዩ ወረዳዎች ለተፈናቀሉ 40 ካህናት የተደረገ ድጋፍ።



ሰቆጣ ለሚገኙ ከወሊጋ ለተፈናቀሉ ወገኞች የተደረገ ድጋፍ



ስልጤ ዞን ቅበት ተፈናቅለው ቡታጅራ ማርያም ይገኙ ለነበሩ ተፈናቃዮች የተደረገ ድጋፍ።



ደቡብ ኦሞ በናጸማይ በድርቅ ለተጎዱት የተደረገ ማኅበራዊ ድጋፍ

**“እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ፤ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም።”**
**ቆላ. ፫ ÷ ፩-፫**

## በዘመነ ትንሣኤ ምን እናድርግ ?

ዘመነ ትንሣኤ የደስታ እና ጸጋ እግዚአብሔር የበዛበት ዘመን በመሆኑ ምክንያት መጾም እና መስገድ የለም። ደስታን እናደርግ ዘንድ እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህቺ ናትና ደስ ሊለን ይገባል። (መዝ ፻፲፯ ÷ ፳፬) በትንሣኤው የተገኘው ደስታ የነፍስም የሥጋም ነው። ማለትም ሥጋ ፈርሶ በስብሶ እንደማይቀር የተረጋገጠበት ነፍስም ከሲዖል ባርነት ነጻ የወጣችበት ነው። ይህም በመሆኑ ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ሥጋም ነፍስም በዘመነ ትንሣኤ ይደሰቱ ዘንድ ትፈቅዳለች።
ይህ ሲባል ግን ሥጋችንን ከመጾም እና ከመስገድ አሳርፈን እንደምናለመልመው ሁሉ ነፍሳችንም በቃለ እግዚአብሔር ፣ በመዝሙር ምስጋና በቅዳሴ እና በምግባረ ሰናይ ልትለመልም ይገባል። የነፍሳችንን ትተን የሥጋችንን ደስታ ብቻ ከፈጸምን ግን የጌታችን ከሞት መነሣት ዓላማ አልገባንም ማለት ነው። የጌታችን ትንሣኤ ዓላማ እኛን ከኃጢአት ውድቀት ማንሣት እንጂ ወደ ኃጢአት ጉድጓድ መጣል አይደለም።

## ሰንበት ትምህርት ቤት እና ክርስቲያናዊ ሕይወት በምን ይገለጻል?

ቤተ ክርስቲያን ስንል ሁሉን ያቀፈች ናት፤ በግልገሎች የተመሰሉ ሕፃናት፣ በጠቦቶች የተመሰሉ ወጣቶችንና በእናት በግ የተመሰሉ ወላጆችን የምታጠቃልል ናት፡፡ ስለዚህ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን መገኘት፣ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት መማር፣ በወንጌል መመራት፣ ሕግጋቱን መጠበቅ፣ እግዚአብሔርን መፍራት፣ ፍቅረ ቢጽ እና ፍቅረ እግዚአብሔርን ማወቅ በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያንን ማወቅ እስከሚፈቀድለት ድረስ ማጥናት አለበት በዚህም ሕይወቱ ይገለጻል፡፡